# መንፈስ ቅዱስ –
## ማንነቱና አገልግሎቱ


ዶክተር ጆን ኤፍ. ዋልቮርድ

Dr. John F. Walvoord



በእንግሊዝኛ ከጻፉት መጽሐፍ

በጌቱ ግዛው የተተረጎመ

ልዩ ረዳት

ትፍስህት ለማ

Published by

LAPSLEY/BROOKS FOUNDATION

Dallas, Texas --- Addis Ababa

U.S.A. Ethiopia

1997 - 1989

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

All Rights Reserved

1989 (1997 እ.አ.አ.)

ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው

"Holy Spirit"

by Dr. John F. Walvoord

ከሚለው መጽሐፍ ሲሆን

የታተመውም በደራሲው ፈቃድ ነው።

Published by

LAPSLEY/ BROOKS FOUNDATION

Dallas, Texas, USA

1997

የላፕስሊ/ብሩክስ ፋውንዴሽን

ስልክ 201464 ፖስታ 41221

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

Addis Ababa Ethiopia

1989

# ምስጋና

ይህ የትርጉም ሥራ ዳር እንዲደርስ ሞያዊ እርዳታ በመስጠት ረገድ የተሳተፉትን ኢትዮጵያውያን በሙሉ፥ በተለይም ጽሑፉን በማረም የረዱንን አቶ ደረሰ ብሩ፥ አቶ ተሾመ ወ/ጻዲቅ፥ አቶ ዘሙይ ሐይሎም፥ አቶ አወቀ ሙሉጌታ፥ እና አቶ ሥዩም ገብረ የሱስን ከልብ እናመሰግናለን።

# መቅድም

በዳላስ ቲዮሎጂካል ሰሚነሪ (Dallas Theological Seminary) ስለ መንፈስ ቅዱስ ባስተማርኩባቸው አያሌ ዓመታት ውስጥ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ አጥጋቢና እውነተኛ ትምህርት የሚሰጡ መጻሕፍት አለመኖራቸውን ተገንዝቤአለሁ።

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ፥ አስፈላጊ የሆኑ ዋና ዋና እውነቶችን ሳያስቀር ስለ መንፈስ ቅዱስ ሰፊና አጠቃላይ ትምህርት ለመስጠት ነው። መጽሐፉ በውስጡ የመጽሐፍ ማውጫ፥ የጥቅስ ማውጫ፥ እና የርእስ ማውጫ ያለው በመሆኑ፥ መጽሐፉ አስፈላጊ የሆኑ አሳቦችን ያለ ችግር በአስፈላጊው ወቅት አውጥቶ ለማጥናት በሚረዳ መንገድ ቀርቧል።

የተፈለገው የቤተ ክርስቲያንን ልዩ ደንብና ወግ ለማስረዳት ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር በመሆኑ ከ1400 የሚበልጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይገኙበታል። የመጽሐፉ መሠረታዊ ዓላማ አንባቢው ስለ መንፈስ ቅዱስ የተሟላ እውቀት እንዲቀስምና ከተሳሳቱ ትምሕርቶች እንዲጠበቅ ነው። በዚህ ጽሑፍ፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በብሉይ ኪዳን፥ የመንፈስ ጥምቀት፥ የመንፈስ ስጦታዎች፥ በመንፈስ ስለመሞላትና ወደፊት ስለሚሆኑ የመንፈስ ትንቢቶች የሚሉት ጉዳዮች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል። እነዚህ ጠቃሚ፥ ነገር ግን የተሳሳተ ግንዛቤ የተሰጣቸው ናቸው። ጸሐፊው ስለ እነዚህ ትምህርቶች በሚያጠግብ ሁኔታ የተዘጋጀ መጽሐፍ ከዚህ ቀደም አላነበበም። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ከቀረበው ትምህርት ሌላ "የመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ ትምህርት ታሪክ" በሚለው ምዕራፍ ይህን መሠረታዊ የእምነት ትምሕርት የሚመለከቱ፥ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ጽሑፎችና የታሪክ ሰነዶች ተሰብስበው ማንም አንብቦ ሊረዳቸው በሚችል ሁኔታ ቀርበዋል። ይህ መጽሐፍ አንባቢው በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተካሄዱትን ታላላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች እንዲረዳ ያስችለዋል።

የመጽሐፉ ዓላማ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ለሚያምኑ ሁሉ ስለ መንፈስ ቅዱስ ማስተማር ቢሆንም፥ የለዘብተኛ (Liberal/ሊበራል)፥ የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት (Neo-Orthodox/ኒዮ-ኦርቶዶክስ) እና የባርት (Barth) ሥነ-መለኮት [theology/ቲያሎጂ] ዘመናዊ አስተያየትና አተረጓጎምንም ያሳውቃል። በዘመናዊ ሥነ-መለኮት የዘመኑን አስተሳሰብ መረዳት የመንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምሕርት ቁልፍ ሲሆን፥ ይህ መሠረታዊ የእምነት ትምሕርትም አስፈላጊ ከሆኑት የትምሕርተ-መለኮት ክፍሎች አንዱ ነው።

ይህን መጽሐፍ ስለ እግዚአብሔር መንፈስ ማወቅ ለሚፈልጉ ሁሉ አበረክተዋለሁ።

ዶክተር ጃን ኤፍ. ዋልቮርድ
Dr. John F. Walvoord

# የመጽሐፍ ማውጫ

## ክፍል አንድ -- የመንፈስ ቅዱስ ተግባራት


### ምዕራፍ አንድ -- የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ........ 23

1. ባሕርያቱ አካላዊ ሕልውና እንዳለው ያረጋግጣሉ ........ 24
2. ሥራዎቹ አካላዊ ሕልውና እንዳለው ያረጋግጣሉ ........ 24
3. በሰብዓዊ ተውላጠ ስም መጠራቱ አካላዊ ሕልውና እንዳለው ያረጋግጥልናል ........ 25
4. መንፈስ ቅዱስ እምነታችንን የምንመሠርትበት፥ ደግሞም የምናምነው አካል ነው ........ 26

### ምዕራፍ ሁለት -- የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት ........ 27

1. መንፈስ ቅዱስ ተለይቶ የሚታወቅባቸው መጠሪያዎች ........ 27
   - የመንፈስ ቅዱስ መጠሪያዎች ከሥላሴ አካላት ጋር ያላቸው ግንኙነት ........ 29
   - ባሕርዩን የሚገልጡ ........ 30
   - ሥራውን የሚገልጡ ........ 31
2. ከእግዚአብሔር ጋር ያለው አንድነትና ግንኙነት ........ 32
   - ከያህዌ ጋር አንድ ስለመሆኑ ........ 32
   - ከአምላክ ጋር አንድ ስለመሆኑ ........ 32
   - መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር ያለው ግንኙነት ........ 33
3. የመንፈስ ቅዱስ ሠራፂነት (መውጣት) ........ 33
   - የመንፈስ ቅዱስ መሥረፅ እርግጠኛነት ........ 34
   - የመንፈስ ቅዱስ ሠራፂነት እርግጠኛ ስለመሆኑ ........ 35
   - የመሥረፅና የመገኘት (የመወሰድ) ግንኙነት ........ 36
   - የመንፈስ ቅዱስ ሠራፂነት ከአብና ከወልድ ስለመሆኑ ........ 36
   - የመንፈስ ቅዱስ ሠራፂነት ከሥራዎቹ ጋር ያለው ግንኙነት ........ 37
4. የመንፈስ ቅዱስ ባሕርያት ........ 37
5. የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ........ 38

### ምዕራፍ ሦስት -- መንፈስ ቅዱስ የተገለጠባቸው አምሳያዎች ........ 41

1. ኃይልን መልበስ ........ 42
2. ርግብ ........ 42

3. የመንፈሱ መያዣ ............ 43
4. እሳት ............ 44
5. ዘይት ............ 45
6. ማኅተም ............ 46
7. አገልጋይ ............ 47
8. ውኃ ............ 47
9. ነፋስ ............ 48

ክፍል ሁለት -- መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን

ምዕራፍ አራት -- መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ ውስጥ ............ 53
1. የመንፈስ ቅዱስ ታዛዥነት ............ 55
2. በመፍጠርና ፍጥረትን በመጠበቅ ተግባር ውስጥ ያለው ድርሻ 56
3. የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ለሁለተኛው የሥላሴ አካል ............ 56
4. የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ለቅዱሳን ............ 57
◆ የዘላለም ሕይወት ............ 57
◆ መገለጥ ............ 57
◆ የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር ............ 58
◆ ማንኛውንም መንፈሳዊ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለን መንፈስ ቅዱስ ነው ............ 59
◆ ቅድስና ............ 59
◆ መማለድ ............ 59
◆ የቤተ ክርስቲያን መመሥረት ............ 60

ምዕራፍ አምስት -- መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር ሥራ ውስጥ ............ 62
1. የመንፈስ ቅዱስ የመፍጠር ሥራ ማረጋገጫዎች ............ 63
◆ የተለዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚሰጡት ማረጋገጫ 63
◆ ኤሎሂም የሚለው ስም አጠቃቀም ............ 65
◆ በፍጥረታት መካከል መሆኑን የሚመለከት አሳብ ............ 66
2. የመንፈስ ቅዱስ የመፍጠር ተግባር ............ 67
◆ ፍጥረትን ሥርዓት የማስያዝ ተግባር ............ 67
◆ ፍጥረታትን የመቅረፅ ተግባር ............ 67
◆ ለፍጥረታት ሕይወትን የመስጠት ተግባር ............ 68
◆ ፍጥረታት የተፈጠሩት ለእግዚአብሔር ክብር ነው ............ 69
3. ፍጥረታትን ጠብቆ የማቆየትና የማደስ ሥራ ............ 70

ምዕራፍ ስድስት -- መገለጥ በብሉይ ኪዳን ........................ 71
1. የመለኮታዊ መገለጥ [Revelation] ዓይነቶች ........................ 71
2. የብሉይ ኪዳን መገለጥ መጠን ........................ 71
◆ ከሙሴ በፊት የነበረ መገለጥ ........................ 72
◆ ከሙሴ እስከ ክርስቶስ ድረስ የተሰጡ መገለጦች ........................ 72
3. የብሉይ ኪዳን ነቢያት ........................ 72
◆ ከአብርሃም በፊት የተሰጠ መገለጥ ........................ 73
◆ ለአብርሃም የተሰጠ መገለጥ ........................ 73
◆ ለሙሴ የተሰጠ መገለጥ ........................ 74
◆ በዘመነ መሳፍንት የተሰጠ መገለጥ ........................ 74
◆ በቀደሙት ነገሥታት ዘመን የተሰጡ መገለጦች ........................ 75
◆ ከምርኮ በፊትና በምርኮ ወቅት የተሰጡ መገለጦች ........................ 76
◆ ምርኮ በኋላ የተሰጡ መገለጦች ........................ 76
4. መገለጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ........................ 77
◆ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚሰጡት ቀጥተኛ ምስክርነት 77
◆ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የተገለጡ ምስክርነቶች ........................ 78
5. መገለጥ የተሰጠባቸው መንገዶች ........................ 79
◆ በንግግር ወይም በቃላት ........................ 79
◆ ሕልም ........................ 80
◆ ራእይ ........................ 81
◆ ተፈጥሮአዊ ባልሆነ እንቅልፍ የሚሰጡ መገለጦች ........................ 81
6. በአዲስ ኪዳን የተሰጡ መገለጦች ........................ 82
◆ በክርስቶስ በኩል የተሰጡ መገለጦች ........................ 82
◆ በአማኞች ውስጥ የተሰጠ መገለጥ ........................ 82
◆ በቅዱሳት መጻሕፍት በኩል የተሰጡ መገለጦች ........................ 82
◆ የመጨረሻዎቹን ቀናት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተሰጡ መገለጦች ........................ 83

ምዕራፍ ሰባት -- መንፈስ ቅዱስ በእስትንፋሰ - እግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ........................ 84
1. የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር አስፈላጊነት ........................ 84
2. የእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ትርጉም ........................ 85
3. እስትንፋሰ-እግዚአብሔር፤ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ........................ 87
◆ የብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች ምስክርነት ........................ 87
◆ የነቢያት የቋንቋ አጠቃቀም ........................ 88
◆ የቅዱሳት መጻሕፍት ርእሶች ........................ 88
◆ የክርስቶስ ምስክርነት ........................ 89
◆ የሐዋርያት ምስክርነት ........................ 89

◆ በንግግር ከተሰጡ መገለጦች ጋር ያለው ተመሳሳይነት ....90
4. የእስትንፋስ-እግዚአብሔር መጠን ....91
◆ ያልታወቀው ያለፈው ጊዜ ....91
◆ ታሪክ ....92
◆ ሕግ ....92
◆ ቃል በቃል መመዝገብ ....93
◆ የአምልኮ ጽሑፎች ....93
◆ ነቢያት ለነበሩበት ዘመን ይሆን ዘንድ የተናገሩት መልእክት ....95
◆ ስለ ወደፊቱ የሚናገሩ ትንቢቶች ....95
5. እስትንፋስ-እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን ....97
◆ እስትንፋስ-እግዚአብሔር በአዲስም ሆነ በብሉይ ኪዳን ውስጥ አንድ ነው ....97
◆ የአዲስ ኪዳን እስትንፋስ-እግዚአብሔርነት በኢየሱስ ክርስቶስ ተረጋግጧል ....98
◆ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የእስትንፋስ-እግዚአብሔር ሥራ መሆናቸውን ሐዋርያት ተናግረዋል ....98
◆ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች የአጠቃቀስ ሁኔታ ለእስትንፋስ-እግዚአብሔር ማረጋገጫ ነው ....99
◆ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ያገኙት ተቀባይነት ....100

## ምዕራፍ ስምንት -- የብሉይ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ለሰው ልጅ ....102

1. ለፍጥረታት ሁሉ የነበረው አገልግሎት ....102
2. የኃያሉ መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር ....103
◆ የብሉይ ኪዳን ካለንበት ዘመን ጋር ሲነጻጸር ....103
◆ ስለ ማደሪያነት የሚናገሩ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ....103
◆ በብሉይ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስ በሰዎች ሕይወት ውስጥ የማደር ልዩ ባሕርያት ....104
3. የመንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ሥራ ....105
◆ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስረጃነት ....106
◆ ኃጢአትን ከመከልከል (ከማቀብ) ጋር የተያያዙ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ....106
4. አብርሆት [Illumination] እና የአገልግሎት ብቃት ....107
◆ የጥበብ ስጦታ ....107
◆ የልዩ ችሎታ ስጦታ ....108
◆ ያልተለመደ የሰውነት ጥንካሬ (ጉልበት) ስጦታ ....108
5. የብሉይ ኪዳን ተአምራት ....109

◆ የብሉይ ኪዳን ተአምራት መጠን ........ 109
◆ መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ከተፈጸሙ ተአምራት ጋር ያለው ግንኙነት ........ 109
◆ መንፈስ ቅዱስ በአዲስ ኪዳን ከተፈጸሙ ተአምራት ጋር ያለው ግንኙነት ........ 110

## ክፍል ሦስት -- መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ጋር ያለው ግንኙነት

ምዕራፍ ዘጠኝ -- መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ መወለድ ጋር ያለው ግንኙነት ........ 115
1. የወንጌላት ባሕርይ ........ 115
◆ የክርስቶስ በሥጋ መምጣት (ተሠገዎ) ........ 116
◆ የሙሴ ሕግ እስከ መስቀሉ ድረስ ቀጥሏል ........ 116
2. የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በወንጌላት ውስጥ ........ 116
◆ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሢሐዊነት ........ 116
◆ መንፈስ ቅዱስ በወንጌላት የነበረው ሥራ የብሉይ ኪዳንን አሠራር የተከተለ ነው ........ 117
3. የክርስቶስ ከድንግል መወለድ ........ 118
◆ ኢየሱስ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነው ........ 118
◆ የክርስቶስ እናት ማርያም ........ 119
4. የኢየሱስ አፀናነስ ሁኔታ ........ 120
◆ የክርስቶስ ሰብአዊነት የመውለድ ወይስ የመፈጠር ውጤት? ........ 120
◆ የክርስቶስ ሰብአዊነት ያለ ኃጢአት ነውን? ወይስ እንዲሁ የተቀደሰ? ........ 121
◆ የአዳም ኃጢአት ወደ ክርስቶስ ተላልፏልን? ........ 123
5. የክርስቶስ ሰብአዊነት ........ 124
◆ የክርስቶስ ሰብአዊነት የተሠራባቸው ነገሮች ........ 125
◆ ኃጢአት የሌለበት ሰብአዊ ተፈጥሮ ........ 125
◆ ሰብአዊ ተፈጥሮው የሰው ልጅ አካላዊ ውሱንነት ነበረው 126
◆ ክርስቶስ የዳዊት ዘር ነው ........ 126
ምዕራፍ አሥር -- መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ሕይወት ... 127
1. መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ የልጅነት ሕይወት ........ 127
◆ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው ከተፀነሰበት ቀን ጀምሮ ነው ........ 127

◆ የክርስቶስ ሰብአዊ ባሕርይ መንፈሳዊ ስጦታዎች በሙሉ ነበሩት ..... 128
◆ የክርስቶስ ሰብአዊ ባሕርይ የሚያድግ ነበር ..... 129
2. መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ጥምቀት አንጻር ..... 130
◆ ጥምቀት መንፈስ ቅዱስ ለክርስቶስ አገልግሎት መስጠት የጀመረበት ጊዜ መግለጫ አይደለም ..... 130
◆ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት አዲስ ምዕራፍ ..... 130
◆ የሥላሴ አንድነት እንደገና መገለጡ ..... 131
3. መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ የነቢይነት አገልግሎት ውስጥ ..... 131
◆ የነቢይነት ስጦታ ዋና ምንጩ መንፈስ ቅዱስ ነው ..... 131
◆ ክርስቶስ ለመስበክ በመንፈስ ቅዱስ ተቀባ ..... 132
4. መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ ከፈጸማቸው ተአምራት ጋር ያለው ግንኙነት ..... 132
◆ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተደረጉ የክርስቶስ ተአምራት 133
◆ ክርስቶስ ተአምራትን በራሱ ኃይል ፈጽሟልን? ..... 133

ምዕራፍ አሥራ አንድ -- መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ሥቃይና ክብር ውስጥ ..... 135
1. መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ሥቃይ ጋር ያለው ግንኙነት ..... 135
◆ ክርስቶስ በምድራዊ ሕይወቱ በደረሰበት ሥቃይ ወቅት መንፈስ ቅዱስ የነበረው አገልግሎት ..... 135
◆ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞት በደረሰበት ሥቃይ መንፈስ ቅዱስ የሰጠው አገልግሎት ..... 136
2. መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ትንሣኤ እና መክበር ጋር ያለውን ግንኙነት በሚመለከት ..... 138
◆ ሥላሴ ከክርስቶስ ትንሣኤ ጋር ያለው ግንኙነት ..... 138
◆ መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ትንሣኤ ጋር ያለው ግንኙነት 138
◆ መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ መክበር ጋር ያለው ግንኙነት 140

ክፍል አራት -- መንፈስ ቅዱስ በደኅንነት ሥራ

ምዕራፍ አሥራ ሁለት -- ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ..... 143
1. መለኮታዊ ቸርነት እና ሉዓላዊነት ..... 143
2. ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ መጠን ..... 143
3. ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ጠቃሚነት ..... 144
4. የጸጋ ለሰው ልጅ አስፈላጊነት ..... 145
5. ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ባሕርያት ..... 146
◆ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያለው ግንኙነት ..... 147

◆ ለዓለም የሚሰጠው የመገለጥ መጠን ..... 150
6. ኃጢአትን የመከልከል ተግባር ..... 152
◆ የመንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ተግባር በብሉይ ኪዳን ..... 152
◆ የመንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን የመከልከል ተግባር በዚህ ዘመን ..... 153
◆ ኃጢአትን በመከልከል ተግባር የሚጠቅሙ ነገሮች ..... 155
7. ለሁሉ የተሰጠ ጸጋ ውሱንነት ..... 155

## ምዕራፍ አስራ ሦስት -- ውጤት አስገኝ ጸጋ ..... 157

1. የትምህርቱ አስፈላጊነት ..... 157
2. ውጤት አስገኝ ጸጋ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ..... 158
3. ውጤት አስገኝ ጸጋ የእግዚአብሔር ሥራ ነው ..... 160
4. የውጤት አስገኝ ጸጋ እርግጠኛነት ..... 161
5. የውጤት አስገኝ ጸጋ መከላከያ ..... 163
◆ የእግዚአብሔር ሥራ የተፈለገውን ውጤት የሚያስገኝ መሆን አለበት ..... 163
◆ የውጤት አስገኝ ጸጋ መሠረታዊ እምነት አስቀድሞ መወሰን ለሚለው ትምህርት በጣም አስፈላጊ ነው ..... 163
◆ ውድቀትና መንፈሳዊ ሞት ውጤት አስገኝ ጸጋን ይሻሉ 164
◆ ከዳግም ልደት ጋር ያለው ተመሳሳይነት ..... 164
6. በውጤት አስገኝ ጸጋ መሠረታዊ ትምህርት ላይ የሚቀርቡ ተቃውሞዎች ..... 165
◆ ከሰው ጥረት አንጻር ..... 165
◆ የሰው ኃላፊነት በተቃራኒው ሲታይ ..... 165
◆ በቂ ጸጋ ለሁሉም ተሰጥቷልን? ..... 166

## ምዕራፍ አሥራ አራት -- ዳግም ልደት ..... 168

1. የዳግም ልደት አስፈላጊነት ..... 168
2. የዳግም ልደት ትርጉም ..... 168
◆ የቃሉ ፍች ..... 168
◆ በሥነ-መለኮት ትምህርት ውስጥ ያለው አጠቃቀም ..... 169
3. ዳግም ልደት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው ..... 171
◆ የእግዚአብሔር ሥራ ..... 171
◆ ለመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ሥራ ነው ..... 171
4. ዳግም ልደት የዘላለምን ሕይወት የማግኘት ሂደት ነው ..... 172
◆ የዘላለም ሕይወት ለዳግም ልደት ማእከሉ ነው ..... 172
◆ አዲስ ልደት ..... 172

- መንፈሳዊ ትንሣኤ ........ 172
- አዲስ ፍጥረት ........ 172
- የዘላለምን ሕይወት የተቀበልነው በእምነት ነው ........ 173

5. ዳግም ልደት የተፈጸመበት የተለየ መንገድ የለም ........ 173
- የካልቪን ሥነ-መለኮት ሊቃውንት ለዳግም ልደት የተለየ መንገድ አለ የሚለውን አሳብ ተቃውመዋል ........ 173
- የሰው ፈቃድ ምንም ውጤት ማምጣት አይችልም ........ 174
- ሌላ መንገድ አያስፈልግም ........ 174

6. ዳግም ልደት በልምምድ የምናረጋግጠው ነገር አይደለም ........ 175
- ልምምድ ዳግም ልደትን ተከትሎ የሚመጣ ነገር ነው ........ 175
- ዳግም ልደት በልምምድ ላይ የሚመሠረት አይደለም ........ 175

7. የዳግም ልደት ውጤት ........ 177
- አዲስ ተፈጥሮ ........ 177
- አዲስ ልምምድ ........ 178
- የዘላለም ዋስትና ........ 179

## ምዕራፍ አሥራ አምስት -- የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ........ 180

1. ለረጅም ጊዜ የታወቁ የአመላካከት ልዩነቶች ........ 180
2. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚፈጸም ነው ........ 182
- ደኅንነትና ጥምቀት የሚነጣጠሉ አይደሉም ........ 182
- ክርስቲያኖች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀዋል ........ 182
- አንዲት ጥምቀት ........ 182
- በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅን እንሻ ዘንድ የተሰጠ ማበረታቻ አይገኝም ........ 183

3. ከክርስቶስ አካል ጋር አንድ ለመሆን መጠመቅ ........ 183
- የአካል አንድነት ........ 183
- የክርስቶስ አካል፥ እጅግ ጠቃሚ የእምነት ትምህርት ........ 183
- በአካሉ ውስጥ ያለው ስፍራ ........ 184

4. ከክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን መጠመቅ ........ 184
- አዲስ ስፍራ ........ 184
- ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን ........ 185
- አዲስ የሕይወት አንድነት ........ 186

5. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በዚህ ዘመን ብቻ ነው ........ 187
- የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለስፍረ-ዘመን ሥነ-መለኮታዊ ትምህርት እጅግ አስፈላጊ ነው ........ 187
- በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ጥቅሶች ........ 187
- የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በልሳን ከመነጋገር ጋር ያለው ግንኙነት ........ 188

◆ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በደኅንነት እምነት ጊዜ የሚፈጸም ነው ........ 189
◆ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አይደጋገምም ........ 189
6. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሕዋሳዊ ልምምድ አይደለም ........ 190
◆ ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጋር የተያያዘ መንፈሳዊ ልምምድ ........ 190
◆ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለአማኞች ሁሉ የሚሆን ነው 190
◆ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የኅብረትን እውነት ያመለክታል ........ 191
◆ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ቅጽበታዊ የእግዚአብሔር ሥራ ........ 191
7. ጥምቀት የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው ........ 191
8. በእሳት መጠመቅ ........ 193
9. በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ ዘላለማዊ ውጤቶች ........ 194
◆ አዲስ አንድነት ........ 194
◆ አዲስ ስፍራ ........ 194
◆ አዲስ ኅብረት ........ 194

## ምዕራፍ አሥራ ስድስት -- የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር ........ 197

1. የመንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ማደር ሁለንተናዊ ነው ........ 197
◆ የመንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ውስጥ አለማደር አለመዳንን ያመለክታል ........ 197
◆ በኃጢአታቸው የቀጠሉ ክርስቲያኖች እንኳ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎች ናቸው ........ 198
◆ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው ........ 198
◆ ጌታ የሚጠብቅብን የሕይወት ደረጃ መለኮታዊ እርዳታን ይጠይቃል ........ 198
2. አስቸጋሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ........ 199
◆ ከስፍረ-ዘመናቸው ይዘት ውጭ ጥቅም ላይ የዋሉ ምንባቦች ........ 199
◆ የሐዋርያት ሥራ 5፡32........ 199
◆ የሐዋርያት ሥራ 8፡14-20........ 200
◆ የሐዋርያት ሥራ 19፡1-6........ 201
◆ በመንፈስ ቅዱስ መቀባት ........ 202
3. የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ የማደር ልዩ ባሕርያት ........ 202
4. መንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ የማደሩ አስፈላጊነት ........ 203

ምዕራፍ አሥራ ሰባት -- የመንፈስ ቅዱስ ማተም ............204
1. ማኅተሙ መንፈስ ቅዱስ ነው ............204
2. የመንፈስ ቅዱስ ማተም ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚሆን ድርጊት ነው ............204
3. በመንፈስ ቅዱስ መታተም ሕዋሳዊ ልምምድ አይደለም ............205
4. በመንፈስ ቅዱስ የመታተም ቁም ነገር ............206

## ክፍል አምስት -- መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ

ምዕራፍ አሥራ ስምንት -- የመንፈሳዊ ስጦታዎች ባሕርይ ............209
1. የመንፈሳዊ ስጦታዎች ጥቅም ............209
2. የመንፈሳዊ ስጦታዎች አጠቃላይ ባሕርያት ............210
3. የመንፈሳዊ ስጦታዎች ልዩ ልዩ ባሕርያት ............212
◆ መንፈሳዊ ስጦታዎች እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ የሚሰጣቸው ናቸው ............212
◆ እያንዳንዱ ክርስቲያን መንፈሳዊ ስጦታዎች አሉት ............213
◆ ስጦታዎች በጠቀሜታ ይለያያሉ ............213
◆ መንፈሳዊ ስጦታዎችን መጠቀም ያለብን በፍቅር ነው ............214
◆ አንዳንድ ስጦታዎች ጊዜያዊ ናቸው ............214
◆ የመንፈሳዊና የተፈጥሮ ስጦታዎች ንጽጽር ............214

ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ -- ቋሚ መንፈሳዊ ስጦታዎች ............215
1. የማስተማር ስጦታ ............215
2. የመርዳት ወይንም የማገልገል ስጦታ ............216
3. የአስተዳደር ወይንም የአገዛዝ ስጦታ ............216
4. የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ ............217
5. የእረኝነት ወይም የመጋቢነት ስጦታ ............217
6. የመምከር ስጦታ ............218
7. የመስጠት ስጦታ ............218
8. ምሕረት የማድረግ ስጦታ ............219
9. የእምነት ስጦታ ............219

ምዕራፍ ሃያ -- ጊዜያዊ መንፈሳዊ ስጦታዎች ............220
1. በአሁኑ ጊዜ ባለው በእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ ያላቸው ተአምራት ስፍራ ............220
◆ የተአምራት እየቀነሱ መሄድ ............220
◆ የተአምራት ዓላማ ............220

◆ የመጽሐፍ ቅዱስ የተአምራት ታሪክ ...... 220
◆ ከአዲስ ኪዳን መሟላት ጋር ያለው ግንኙነት ...... 221
◆ ቅዱሳት መጻሕፍት ከልምምዶች ሲነጻጸሩ ...... 221
2. የሐዋርያነት ስጦታ ...... 222
◆ የሐዋርያነት አገልግሎት መጠን ...... 222
◆ ለሐዋርያነት አገልግሎት ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎች ...... 223
◆ ሐዋርያነት ስጦታ ነው ...... 224
3. የነቢይነት ስጦታ ...... 225
◆ የነቢይነት ስጦታ መጠን ...... 225
◆ የአዲስ ኪዳን ነቢይ ባሕርያት ...... 225
◆ በነቢይነት ስጦታ ውስጥ ያሉ ነገሮች ...... 225
◆ በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የነቢይነት ስጦታ አስፈላጊነት ...... 226
◆ የነቢይነት ስጦታ ጊዜያዊ ባሕርይ ...... 227
4. ተአምራት የማድረግ ስጦታ ...... 227
◆ ተአምራት ማድረግ አነስተኛው ስጦታ ነው ...... 227
◆ ተአምራትን የማድረግ ስጦታ በሐዋርያት ዘመን መጨረሻ ላይ አብቅቷል ...... 228
◆ ስጦታው ያበቃ ቢሆንም ተአምራት ቀጥለዋል ...... 228
5. የፈውስ ስጦታ ...... 228
6. በልሳናት የመናገር ስጦታ ...... 229
◆ ችግሩን መግለጥ ...... 229
◆ ለችግሩ የተለያዩ መፍትሔዎች ...... 231
◆ ለችግሩ መፍትሔ ለማስገኘት የሚጠቅም መመሪያ ...... 232
◆ በሐዋርያት ሥራ የተገለጠው ልሳን ጠቃሚነቱ እንደ ምልክት ማገልገሉ ነው ...... 233
◆ በልሳን መናገር በ1ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ ...... 234
◆ በልሳን መናገር ጊዜያዊ ስጦታ ነበር ...... 236
7. በልሳን የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ ...... 238
8. መናፍስትን የመለየት ስጦታ ...... 238

## ምዕራፍ ሃያ አንድ -- የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ባሕርይ ...... 240

1. የትምህርቱ መሠረታዊ አስፈላጊነት ...... 240
2. የመንፈሳዊ ልምምድ ተቀዳሚ ምንጭ ...... 240
3. የተለያዩ መንፈሳዊ ልምምዶች ...... 241
4. መንፈሳዊነት ከብስለት ጋር ሲነጻጸር ...... 241
5. በውስጣችን ያደረውና ሊታገድ የማይችለው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ...... 243
6. በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ትእዛዝ ...... 245

7. የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በተደጋጋሚ የሚፈጸም ልምምድ ነው ....... 246

ምዕራፍ ሃያ ሁለት -- ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚያስፈልጉ ነገሮች ....... 249

1. መንፈስን አታጥፉ ....... 249
   - ፍች ....... 249
   - የሰይጣን ኃጢአት ....... 250
   - ራስን የመስጠት የመጀመሪያ ተግባር ....... 250
   - ያለማቋረጥ ራስን የመስጠት ሕይወት ....... 251
   - የክርስቶስ ታላቅ ምሳሌነት ....... 253
2. መንፈስን አታሳዝኑ ....... 253
   - ፍች ....... 253
   - መፍትሔው ኃጢአትን መናዘዝ ነው ....... 255
   - ያለማቋረጥ በኃጢአት ስለ መኖር የተሰጠ ማስጠንቀቂያ 257
3. በመንፈስ ተመላለሱ ....... 258
   - ፍች ....... 258
   - የክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት መለኪያ ....... 259
   - የዓለም አሠራር ኃይል ....... 260
   - የሰይጣን ኃይል ....... 260
   - ኃጢአታዊ ተፈጥሮ ....... 261
   - የፍጹምነት ፅንሰ-አሳብ ....... 262
   - የቅድስና ፅንሰ-አሳብ ....... 264
   - የኃጢአትን ባሕርይ የመደምሰስ (ከሥሩ ነቅሎ የመጣል) ፅንሰ-አሳብ [Eradication/ኢራዲኬሽን] ....... 269
   - ለራስ የመሞት ንድፈ አሳብ ....... 272
   - የሥጋ ፍጹም ደካማነት ....... 273
   - የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆን ....... 273

ምዕራፍ ሃያ ሦስት -- የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውጤቶች ....... 275

1. ልምምዳዊ ቅድስና ....... 275
2. ማስተማር ....... 276
3. ምሪት (አመራር) ....... 277
4. ዋስትና ....... 278
5. አምልኮ ....... 278
6. ጸሎት ....... 279
7. አገልግሎት ....... 280

## ክፍል ስድስት -- የመንፈስ ቅዱስ ትንቢቶች

### ምዕራፍ ሃያ አራት -- መንፈስ ቅዱስ በታላቁ መከራ ዘመን


.......... 283

1. የዚህ የእምነት ትምህርት ቸል መባል .......... 283
2. በደኅንነት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ .......... 284
   - በታላቁ መከራ ዘመን ብዙዎች ይድናሉ .......... 284
   - የኢዩኤል ትንቢት .......... 285
   - የእስራኤል ተስፋ .......... 286
3. የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በታላቁ መከራ ጊዜ በሚኖሩት አማኞች ሕይወት .......... 287
4. በታላቁ መከራ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውሱን ነው .......... 288


### ምዕራፍ ሃያ አምስት -- መንፈስ ቅዱስ በሺሁ ዓመት መንግሥት .......... 289


1. መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን በመከላከል ተግባር .......... 289
2. የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በደኅንነት ውስጥ .......... 290
3. በሺህ ዓመቱ መንግሥት መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ውስጥ .......... 290


## ክፍል ሰባት -- ታሪክ

### ምዕራፍ ሃያ ስድስት -- የመንፈስ ቅዱስ ትምህርተ-ሃይማኖት አጭር ታሪክ .......... 295


1. ቅድመ ኒቅያ ዘመን .......... 296
2. የኒቅያ ዘመን .......... 299
3. የድህረ ኒቅያ ዘመን .......... 301
4. መካከለኛው ዘመን .......... 302
5. የቅድመ ተሐድሶ ዘመን .......... 304
6. የፕሮቴስታንት ተሐድሶ .......... 306
7. ድህረ ተሐድሶ ወቅት .......... 308
8. መንፈስ ቅዱስ በአሁኑ ዘመን .......... 311


### ምዕራፍ ሃያ ሰባት -- መንፈስ ቅዱስ በዚህ ዘመን ባሉ የሥነ-መለኮት ትምህርቶች ውስጥ .......... 315


1. መንፈስ ቅዱስ በለዘብተኝነት የሥነ-መለኮት ትምህርት ውስጥ . .......... 315

◆ የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ..................... 315
◆ እግዚአብሔር አብሮን ስለመሆኑ የተሰጠ ትኩረት ..................... 316
◆ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይልን ወይም ልዕልናን መካድ ..................... 317
◆ የተአምራዊ መገለጥ ወደ ሰብአዊ ግኝት ዝቅ ማለት ..................... 317

2. የካርል ባርት ሥነ-መለኮት ..................... 317
◆ ባርት ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ያለው አመለካከት ..................... 318
◆ ባርት ስለ መንፈስ ቅዱስ ፈጣሪነት ያለው አመለካከት ..................... 319
◆ ስለ መንፈስ ቅዱስ አስታራቂነት የባርት አመለካከት ..................... 321
◆ የባርት አመለካከት ስለ መንፈስ ቅዱስ የመቤዠት ሥራ ..................... 321
◆ የባሪቲያኒዝም ጉድለቶች ..................... 322

3. መንፈስ ቅዱስ በአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት የሥነ-መለኮት ትምህርት ..................... 323
◆ የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት እንቀስቃሴ ..................... 323
◆ የአዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት የሥነ-መለኮት ትምህርት በአጠቃላይ ሲታይ ..................... 324
◆ አዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ያለው አመለካከት ..................... 325
◆ አዲሱ-ቀጥተኛ ሃይማኖት ስለ መገለጥ ያለው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ..................... 327

4. ማጠቃለያ ..................... 331

## ክፍል ስምንት - - መረጃዎች

**የእንግሊዝኛ ስሞችና ሌሎች ቃላት** ..................... 335

**የሥነ-መለኮት ትምህርቶች መግለጫ** ..................... 341

**የአርእስቶች ማውጫ** ..................... 347

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማውጫ** ..................... 357

**በቅርብ የተደረጉ የእምነት መግለጫዎች** ..................... 369

# መንፈስ ቅዱስ –

## ማንነቱና አገልግሎቱ

# ማሳሰቢያ

- የመጽሐፉ ተርጓሚ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ አንዳንድ ክፍሎችን ግልጥ ለማድረግ ሲል በደራሲው ፈቃድ አንዳንድ ማብራሪያዎችን ጨምሯል።
- የተጠቀሱት ጊዜያት የተመለከቱት በአውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ነው።
- "መጽሐፍ ቅዱስ" እና "ቅዱሳት መጻሕፍት" የሚሉትን ቃላት በማፈራረቅ ተጠቅመንባቸዋል። የሚያካትቱትም የብሉይ ኪዳንን ሠላሳ ዘጠኝ መጻሕፍትና በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙትን ሃያ ሰባት መጻሕፍት ነው።
- በዚህ መጽሐፍ፥ ከመዝሙረ ዳዊት ከምዕራፍ 10-146 ውስጥ የተጠቀሱ ጥቅሶች ሁሉ ከድሮው (1954 ዓ.ም.) መጽሐፍ ቅዱስ በቅንፍ የተጠቀሱትን ምዕራፎች ያመለክታሉ።
- የሥነ-መለኮት ትምህርቶችን የሚያመለክቱ ቃላትና ስሞች አጭር ማብራሪያ በጽሑፉ መጨረሻ በመረጃዎች ዝርዝር ላይ ቀርቧል።
- በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ ከሚገኙበት የገጽ ቁጥር ጋር በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ በ"ጥቅስ ማውጫ" ላይ ቀርበዋል።

  እንዲሁም በመጽሐፉ ውስጥ ማብራሪያ የተሰጠባቸው አርእስቶች በመጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙበት ቦታ ጋር በ"አርእስቶች ማውጫ" ላይ ይገኛሉ።

  የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች እነዚህ ሁለት ማውጫዎች ለጥናታቸው ጠቃሚ ሆነው ያገኟቸዋል ብለን እናምናለን።
- ተጨማሪ ጥናት ለማድረግ የሚፈልጉ ሰዎችን ለመርዳት ሲባል አንዳንድ ስሞችና አገላለጦች በጽሑፉ ለመጀመሪያ ጊዜ በተከሰቱ ወቅት በእንግሊዝኛ በቅንፍ ተመልክተዋል። አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜም የቃላቱ የአማርኛ አነባበብ በቅንፉ ውስጥ ታክሏል። የሁሉም ቃላት ዝርዝር በፊደል ቅደም ተከተል በመጽሐፉ መጨረሻ ይገኛል።

# — ክፍል አንድ —

# የመንፈስ ቅዱስ ተግባራት

# 1

# የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና

እግዚአብሔር አብና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የየራሳቸው የሆነ አካላዊ ሕልውና እንዳላቸው ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስም የራሱ የሆነ አካላዊ ሕልውና አለው። ይህም እውነት የቅዱሳት መጻሕፍት መሠረታዊ መገለጥ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት መንፈስ ቅዱስ ልክ እንደ አብና እንደ ወልድ እውነተኛ የመለኮትነት ባሕርይ እንዳለውና እንደ እግዚአብሔር ሊመለክ፥ በታላቅነት ሊከበር፥ ሊወደድና ሊታዘዙት እንደሚገባ ያሳያሉ። መንፈስ ቅዱስን ከዚህ በተለየ መንገድ መመልከት በእግዚአብሔር ላይ ክፉ ነገርን እንደ መናገር (እንደ መሳደብ) እና እንደ አለማመን የሚቆጠር በደል ነው። ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት በማሰብ በዚህ በተቀደሰና ውድ በሆነ እውነት ላይ በመመሥረት እንቆማለን።

የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ጉዳይ ለብዙ ዘመናት በተለያዩ የክርስትና እምነት ክፍሎች (አብያተ ክርስቲያናት) ዘንድ የተካደና ችላ ተብሎ የተተወ ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል። በ20ኛው ክፍለ-ዘመን ክርስቲያኖች ዘንድም ቢሆን የተስተዋለ አልነበረም። ስለ ክርስቶስና ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረው ትምህርት ላይ ብርቱ ተቃውሞንና ዓመፅን ያነሣሣው መናፍቁ አርዮስ [Arius] የክርስቶስን ዘላለማዊነትና የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ ሕልውና ክዷል። መንፈስ ቅዱስ ለአርዮስ በዚህ በተፈጠረው ዓለም የተገለጠ "ከእግዚአብሔር የሚወጣ ኃይል" ብቻ ነው። የአርዮስ አቋም በ325 ዓ.ም. በተካሄደው የኒቅያ ጉባኤ [Council of Nicea] የተወገዘ ቢሆንም፥ አሳቡ ከእርሱ ቀጥሎ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በሳቱ ትምህርቶችም ታይቷል። በ16ኛው ክፍለ-ዘመን ሱስንዮስ [Socinius] እና ተከታዮቹ መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የወጣ ዘላለማዊው ኃይል ነው የሚል አቋም ያዙ። ይህም አቋም የሥላሴን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ለማይቀበለው ዘመናዊ የዩኒተሪያኒዝም [Unitarianism] አሳብ መሠረት ሆነ። በየዘመናቱ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጡ መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች እጅግ የተለያዩ ቢሆኑም፥ አብዛኞዎቹ ወግ አጥባቂነትን የሚያንጸባርቁ ናቸው። ቀጥተኛ አቋም አላቸው የሚባሉት ክርስቲያኖች፥ በቅዱሳት መጻሕፍት በተሰጠው መገለጥ መሠረት መንፈስ ቅዱስ የራሱ የሆነ አካላዊ ሕልውና ያለው መሆኑን ይቀበላሉ።

## 1. ባሕርያቱ አካላዊ ሕልውና እንዳለው ያረጋግጣሉ

መንፈስ ቅዱስን በሚመለከት ከሁሉም አንጻር የሚሰጡ መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች አካላዊ ሕልውናውን የሚመሰክሩ ቢሆ ኑም፥ በተለይ ስለ ባሕርዩ የሚደረግ ጥናት ይህን ጉዳይ ያለ አንዳች ማወላወል ያረጋግጣል። አንድ ነገር የራሱ የሆነ አካላዊ ሕልውና አለው ለማለት የሚቻለው እውቀት፥ ስሜት እና ፈቃድ ሲኖሩት ነው። መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ነገሮች በሙሉ ያሟላል። እውቀቱ በአስደናቂ ሥራዎቹ ሁሉ ውስጥ ተገልጧል። ለዚህ ነው ስለ መንፈስ ቅዱስ በግልጥ እንዲህ የተባለው:- "መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና፥ ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው። በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም" (1ኛ ቆሮ. 2፡10-11)። እርሱ የጥበብ መንፈስ ነው (ኤፌ. 1፡17)፥ የጥበብ እና የማስተዋል መንፈስ፥ የምክርና የኃይል መንፈስ፥ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ነው (ኢሳ. 11፡2)። ኃጢአት እንደሚያሳዝነው የተገለጠበት ክፍል ደግሞ ስሜት እንዳለው ያሳየናል (ኤፌ. 4፡ 30)። በሁሉን ቻይነቱ ለእያንዳንዱ "እርሱ እንደሚፈቅድ" መንፈሳዊ ስጦታን እያካፈለ እንደሚሰጥ መገለጡ ፈቃድ እንዳለው የሚያሳይ ነው (1ኛ ቆሮ. 12፡11)። እነዚህ አንድ አካላዊ ሕልውና ያለው ነገር ባሕርያት፥ በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ እንዳሉ ማረጋገጥ ማለት፥ ሰፊ እና እጅግ አጠቃላይ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስን መለኮታዊነት የሚመለከት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ማረጋገጥ ማለት ነው። እግዚአብሔር የራሱ የሆነ አካል ካለውና መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ከሥላሴ አካላት አንዱ ከሆነ፥ እርሱም የራሱ የሆነ አካል አለው ማለት ነው። የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ ሕልውና መካድ ማለት፥ የሥላሴን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት መካድ ማለት ነው።

## 2. ሥራዎቹ አካላዊ ሕልውና እንዳለው ያረጋግጣሉ

መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና እንዳለው የምናረጋግጥባቸውና ከሁሉም የተሻለ ተጨባጭ ማስረጃ ሆነው ወደ ውሳኔ እንድንደርስ የሚረዱን ሥራዎቹ ናቸው። ሥራዎቹን ተመልክተን መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና እንዳለው ባንቀበል፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደሚገባ ልንተረጉ ማቸውና ልንረዳቸው አልቻልንም ማለት ነው ። የመንፈስ ቅዱስን ሥራዎች ወደፊት በሰፊው የምንመለከት ስለሆነ፥ ለጊዜው በአስረጅነት ብቻ ጥቂቶቹን እንጠቅሳለን። የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች በሙሉ አካላዊ

ሕልውናን የሚጠይቁ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር ሥራ ውስጥ የነበረው ተግባር (ዘፍጥ. 1፡2)፥ ኃይል የመስጠት (ዘካ. 4፡6)፥ የማስተማር (ዮሐ. 16፡13)፥ የመምራት (ኢሳ. 48፡16፤ ሮሜ 8፡14) ፥ የማጽናናት (ዮሐ. 14፡26)፥ የመጸለይ (ሮሜ 8፡26)፥ ስለ ኃጢአት፥ ስለ ጽድቅ እና ስለ ፍርድ ዓለምን የመውቀስ (ዮሐ. 16፡8)፥ ኃጢአትን የመከልከል (ዘፍጥ. 6፡3፥ ኢሳ. 59፡19፤ 2ኛ ተሰ. 2፡7)፥ የማዘዝ እና (2ኛ ተሰ. 2፡7፤ ሐዋ. 8፡29፤ 13፡2፤ 16፡7) የመሳሰለው ሥራ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ አካላዊ ሕልውና እንዳለው ያሳያል። የራሱ አካላዊ ሕልውና የሌለው ወይም ከሌላ የወጣ ነገር፥ ሊፈጥር፥ ኃይል ሊሰጥ፥ ሊያስተምር፥ ሊመራ፥ ሊጸልይም ሆነ ሊያዝ አይችልም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ ሕልውና የተቃወሙ ሰዎች፥ በትምህርታቸው ለመጽናት ሲሉ መጽሐፍ ቅዱስ፥ ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የጻፉት መሆኑንና ምንም ስሕተት የሌለበት የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን መካድ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተውታል።

## 3. በሰብአዊ ተውላጠ ስም መጠራቱ አካላዊ ሕልውና እንዳለው ያረጋግጥልናል

በዕለት ተዕለት ንግግር ውስጥ እንደ እኔ፥ እርሱ፥ እርስዋ፥ እነርሱ፥ የመሳሰሉት ሰብአዊ ተውላጠ ስሞች የሚያገለግሉት ለሰዎች ነው። በሥነ-ጽሑፍ ዓለም ነገሮችን በሰዎች መስሎ መናገር በጣም የተለመደ በመሆኑ፥ ትርጉሙ ግልጥ ያልሆነና ጥርጣሬ ላይ የሚጥል አይደለም። መንፈስ ቅዱስም አካላዊ ሕልውናውን በሚያረጋግጥ መልኩ በሰብአዊ ተውላጠ ስሞች ተጠርቷል። በአዲስ ኪዳን የግሪኩ ቃል *'ኒዩማ'* ['pneuma'] (ማለት መንፈስ) የአንስታይም ሆነ የተባዕታይ ፆታን ያልያዘ (ግዑዝ ፆታ ወይም "Neuter/ኑተር") ስም ነው። ይህ ስም ብዙ ጊዜ አንስታይም ተባዕታይም ካልሆነ ተውላጠ ስም ጋር በመቀናጀት ጥቅም ላይ ይውላል። ቢሆንም በአንዳንድ ስፍራዎች ከተባዕታይ ተውላጠ ስም ጋር በመያያዝ ተጠቅሶ ይገኛል (ዮሐ. 15፡26፤ 16፡13-14)። ተባዕታዩ ተውላጠ ስም በነዚህ ክፍሎች የመንፈስን አካላዊ ሰብእና ያመለክታል። በተመሳሳይ መንገድ "እርሱም" የሚል ተውላጠ ስም ተሰጥቶት እናያለን (ኤፌ. 1፡13-14)። ይህም ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና እንዳለው መቆጠሩን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያስረዳ ነው። ቻርልስ ሆጅ [Charles Hodge] እንዳለው፦ "መንፈስ ቅዱስ እንደ አካል በግጥም፥ በቅኔ ወይም ስሜትን በሚቀሰቅሱ ንግግሮች ሳይሆን፥ በቀላል ትረካዎች እና በማስተማሪያ መመሪያዎች (ትእዛዞች) ውስጥ ተገለጠ።

አካላዊነቱም እርስ በእርስ በሚደጋገፉ ብዙ መረጃዎች ተረጋግጧል። ስለዚህ የሰብአዊ ተውላጠ ስሞችን አጠቃቀም በሚመለከት መንፈስ ቅዱስን በሰው ምሳሌነት መግለጥ ነው እንጂ፥ አካላዊነቱን ማሳየት አይደለም ማለት፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን የመተርጎም ሕጎችን ሁሉ መጣስ ነው።"

## 4. መንፈስ ቅዱስ እምነታችንን የምንመሠርትበት፥ ደግሞም የምናምነው አካል ነው

እውነትን አገናዝቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስ የሚያምኑበት አካል እንደሆነ ያስተውላሉ። ይኸውም አውጥተው አውርደው በማሰብ ሳይሆን፥ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያላቸው ኅብረት ወደዚህ መረዳት በቀጥታ ስለሚያመጣቸው ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አባባል በመንፈስ ቅዱስ ላይ ኃጢአት መሥራት (ማለት እርሱን ማስመረር) (ኢሳ. 63፡10)፥ ማሳዘን (ኤፌ. 4፡30)፥ ትቶ እንዲሄድ ማድረግ (መዝ. 51፡11) እንዲሁም ለእርሱ መታዘዝ (ሐዋ. 10፡19-21) ይቻላል። በእነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት መንፈስ ቅዱስ የምናምነው አካል መሆኑን ሳይረዱ ማለፍ የማይቻል ነው። ይህ እውነት በማቴዎስ 28፡19 ስለ ጥምቀት በተነገረው መሠረታዊ ደንብ ውስጥ አካላዊ ሕልውናቸው ተቀባይነት ካገኘው ከአብና ከወልድ ጋር መንፈስ ቅዱስም በእኩልነት በመቅረብ እንደገና ተረጋግጧል። እንደዚሁም በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፡14 የተጻፈው የሐዋርያት ቡራኬ የሥላሴን አካላት እኩልነት ያመለክታል።

የቅዱሳት መጻሕፍትን መገለጥ ለሚቀበሉ ሁሉ፥ ተአማኒነት ያለው ብቸኛ አቋም፥ በመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ሙሉ ለሙሉ ማመን ነው። ይህ አቋም ከመነሻው ጀምሮ የእውነተኛ ክርስቲያኖች አቋም ነበር። ቻርልስ ሆጅ እንዳለው:- "የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና ከመነሻው ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን እምነት ነበር። ምስቅልቅሉ በወጣው የሥነ-መለኮት ትምህርት ዘመን ይህን እውነት የተቃወሙ ጥቂት ወገኖች ቢኖሩም፥ በዘመናችን ከሱስንያውያን [Socinians]፥ ከአርዮሳውያን [Arians] እና ከሰባሊዮሳውያን [Sabellians] በስተቀር ይህን እውነት የካደ የለም።"

# 2

# የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት

የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት ከጥንት ጀምሮ በክርስትና እምነት ውስጥ ዋና መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ነው። በአራተኛው የክርስትና ክፍለ-ዘመን አርዮሳውያን ያስነሡት ተቃራኒ ትምህርት፥ የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውናና አምላክነት፥ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በእውነተኛው የክርስትና መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ የተረጋገጠ እንዲሆን አደረገ። አርዮስ በመጀመሪያ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ ሕልውና ተቀብሎ ነበር። በኋላ ግን የመንፈስ ቅዱስን አካላዊ ሕልውናም ሆነ መለኮታዊነት ካደ። በርሱ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሌሎች የክርስትና እምነት መሪዎች አርዮስን ስላወገዙት በመናፍቅነቱ የታወቀ ሆነ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውናም ሆነ መለኮትነት በእውነተኛው የክርስትና ትምህርት ውስጥ ተረጋገጠ። ሆጅ እንደገለጠው:- "ከ4ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና እንዳለው የተቀበሉ ሁሉ አምላክነቱን ለመካድ ቃጥቷቸው አያውቅም።"

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት የሚያረጋግጡ እጅግ ብዙ መረጃዎች አሉ። በአጠቃላይ ይህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት፥ መንፈስ ቅዱስ በተሰጡት ስሞችና በሚታወቅባቸው መለያዎች፥ ከእግዚአብሔር ጋር ባለው አንድነቱ፥ በሥላሴ ውስጥ ባለው ግንኙነትና በሠራፂነቱ (በመውጣቱ)፥ በመለኮታዊ ባሕርዩና በተለያዩ መለኮታዊ ሥራዎቹ ሁሉ የተረጋገጠ ነው። እነዚህ መረጃዎችና እውነቶች በአንድነት ሲሆኑ ለመንፈስ ቅዱስ አምላክነት እጅግ ጠንካራ የቅዱሳት መጻሕፍት ምስክሮች ይሆናሉ።

## 1. መንፈስ ቅዱስ ተለይቶ የሚታወቅባቸው መጠሪያዎች

መጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተሰጡትን ገለጣዎች በምንመረምርበት ጊዜ ማንኛውንም ሁለተኛ አካል የምንጠራበት፥ ለምሳሌ እንደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዓይነት ቋሚ ስም እንደሌለው እንገነዘባለን። ነገር ግን ማንነቱን በሚገልጡ የተለያዩ መለያዎች ተጠርቶ እናየዋለን። ከእነዚህም አንዱ በቅዱሳት መጻሕፍትም ሆነ በተለምዶ ብዙ ጊዜ የምንጠቀምበት "መንፈስ ቅዱስ" የሚለው

መጠሪያ ነው። አካላዊ ሕልውናው ምንም ዓይነት ቁሳዊ ነገር የሌለበት ንጹሕ በመሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት ‘‘መንፈስ’’ ተብሎ ተጠርቷል። ‘‘ቅዱስ’’ የሚለው ገላጭ ቅጽል፥ ፍጡራን ከሆኑ ከሌሎች መናፍስት የተለየ መሆኑን ያሳየናል።

ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፥ መንፈስ ቅዱስ በተለያዩ መጠሪያዎች የመጠቀሱ ጉዳይ ሲጠና፥ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ አንዳንድ እውነቶችን ያመለክታል። መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን የመጀመሪያ ቋንቋ ስንመለከት፥ ከዚህ ሌላ በሌሎች መጠሪያዎቹ እንደተጠቀሰ እናያለን። ስለሆነም በብሉይ ኪዳን ‘ሩአክ’ [‘ruack’] የሚለው ቃል ከመቶ ጊዜ በላይ መንፈስ ቅዱስን ለመግለጥ ተጽፏል። መጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ ከተጻፈበት ቋንቋ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች ሲተረጎም፥ ለአንዳንድ ቃላቶችና አባባሎች ተመጣጣኝ የሆነ ትርጉም ማግኘት አስቸጋሪ ስለሆነ፥ መጠነኛ የሆነ የትርጉም ልዩነት ይኖራል። ያም ሆነ ይህ በርከት ባሉ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ብዙ ጊዜ ስለ መንፈስ ቅዱስ ተጽፎ ይገኛል። ከሚንግስ [Cummings] የተባለው የሥነ-መለኮት ሊቅ በብሉይ ኪዳን ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገሩ ሰማንያ ስድስት መግለጫዎችን (ጥቅሶችን) በመዘርዘር ይጠቅሳል። ከሚንግስ በዝርዝር ሲያቀርበው፥ መንፈስ ቅዱስ ዘሌዋውያንን ሳይጨምር ‘‘ፔንታቱክ’’ [Pentateuch] ተብለው በሚጠሩት አምስት የሙሴ መጻሕፍት 14 ጊዜ፥ በትንቢተ ኢሳይያስ 13 ጊዜ፥ በትንቢተ ሕዝቅኤል 15 ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፥ በአጠቃላይ ከሠላሳ ዘጠኙ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መካከል በሀያ ሁለቱ ውስጥ መጠቀሱን እናያለን። ከሚንግስ እነዚህ ክፍሎች ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገሯቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ሲያጠቃልል እንዲህ ብሏል:-

> ‘‘ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መንፈስ ቅዱስ የጠቀሱበት ክፍልና ቁጥር ብዛትም ሆነ ግልጥነት ስለ መጻሕፍቱ ባሕርይ የሚያሳየው የተለየ ነገር አለ ለማለት አንችልም። በተጠቀሱበት የዘመናት ቅደም ተከተልም የተለየ ግንኙነት ለመኖሩ ምንም ማረጋገጫ የለም። ይህም ማለት ስለ መንፈስ ቅዱስ ብዙ ጊዜ የተጠቀሱ እንደ ትንቢተ ኢሳይያስ (750 ዓ.ዓ.)፥ ትንቢተ ሕዝቅኤል (590 ዓ.ዓ.) እና የሙሴ መጻሕፍት (1450 ዓ.ዓ.) ያሉት በተጻፉበት ዘመን ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ የተለየ ነገር ስለመኖሩ የሚያረጋግጥ አይደለም። ብዙ ጊዜ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተጻፉ መጻሕፍት ከሌሎቹ ጋር ሲወዳደሩ ይበልጥ መንፈሳዊ ናቸው ማለትም አይደለም። ስለ መንፈስ ቅዱስ በብዛት በመጥቀስ የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘው ሕዝቅኤል፥ ቀጥሎ መጽሐፈ መሳፍንት (ሰባት ጊዜ)፥ መዝሙረ ዳዊት (ስድስት ጊዜ)፥

ዘዳግም (አንድ ጊዜ)፥ 2ኛ ዜና (አራት ጊዜ) መሆኑ መንፈሳዊነታቸውን የሚያሳይ ቅደም ተከተል አይሆንም። ነገር ግን እያንዳንዱ የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊ ልዩ ትኩረት ከሚሰጥበት ጉዳይ አኳያ ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውናም ሆነ ሥራ በመጽሐፉ አስፍሮ እናገኛለን። በትንቢተ ሕዝቅኤል ስለ መንፈስ ቅዱስ ከተጠቀሱባቸው አሥራ አምስት ክፍሎች ስድስቱ የሚናገሩት፥ መንፈስ ቅዱስ ነቢዩን ወደሚፈልገው ቦታ እንደወሰደው ነው። በመጽሐፈ መሳፍንት ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገሩት ሰባት ክፍሎች ደግሞ፥ መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች የሰጠውን ኃይልና ብርታት የሚገልጡ ናቸው። በአሪት ዘጸአት መንፈስ ቅዱስ ትኩረት ተሰጥቶት በተለይ የቀረበው የጥበብ መንፈስ ሆኖ ነው። በመጽሐፈ ሳሙኤልና ዜና መዋዕል፥ መንፈስ ቅዱስ ለነቢያት መገለጥንና መልእክትን የሚሰጥ ሆኖ ቀርቧል። በትንቢተ ኢሳይያስና በመዝሙረ ዳዊት ስለ መንፈስ ቅዱስ የቀረቡት ሁለት ዋና ዋና ትምህርቶችም ከመሢሑ ጋር ያለውን ግንኙነትና የራሱን የግል ባሕርይ፥ ማለትም እንደሚያዝን፥ በዓመፅና በሚገባ ባለመከበሩ ምክንያት እንደሚቆጣና እንደሚመረር ወዘተ. . . የሚናገሩ ናቸው።”

በአዲስ ኪዳን ስለ መንፈስ ቅዱስ የተጠቀሱ ክፍሎች በብሉይ ኪዳን ከተጠቀሱት ይበልጣሉ። ከሚንግስ ባደረገው ጥናት መሠረት፥ አዲስ ኪዳን መጀመሪያ በተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ የመንፈስ ቅዱስ መጠሪያ የሆነውና ‘ኒዩማ’ የሚለው ቃል በሁሉም የአዲስ ኪዳን ዋና ዋና መጻሕፍት ውስጥ ባጠቃላይ 261 ጊዜ ተጠቅሶአል። ከሚንግስ ጥናቱን በዝርዝር ሲያቀርብ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ በአራቱ ወንጌላት አምሳ ስድስት ጊዜ፥ በሐዋርያት ሥራ አምሳ ሰባት ጊዜ፥ በጳውሎስ መልእክቶች አንድ መቶ አሥራ ሦስት ጊዜና በቀሩት መጻሕፍት ሠላሳ ስድስት ጊዜ ተጠቅሷል ብሏል። ከዚህ ጭብጥ የምንረዳው፥ ከዘፍጥረት 1፡2 ጀምሮ እስከ ራእይ 22፡17 ያለማቋረጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ መነገሩን ነው። ይህም የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በየዘመናቱ በቋሚነት እንደሚኖር ወይም ሕያው እንደሆነ ያሳየናል። የመንፈስ ቅዱስ መጠሪያ ስሞች መሠረታዊ እውነቶችን ያዘሉ በመሆናቸው፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ ትምህርት መሠረት ለመጣል ይረዳሉ።

*የመንፈስ ቅዱስ መጠሪያዎች ከሥላሴ አካላት ጋር ያላቸው ግንኙነት።* መንፈስ ቅዱስን ከሚመለከቱ በርከት ያሉ ልዩ ልዩ ስያሜዎች አሥራ ስድስት ያህሉ ከሌሎች የሥላሴ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት ይገልጣሉ። ከእነዚህ መካከል አሥራ አንዱ መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚገልጡ ናቸው። 1. የእግዚአብሔር መንፈስ

(ዘፍጥ. 1፡2፤ ማቴ. 3፡16)፥ 2. የጌታ መንፈስ (ሉቃስ 4፡18)፥ 3. የአምላካችን መንፈስ (1ኛ ቆሮ. 6፡11)፥ 4. መንፈሱ (ዘኁል. 11፡29)፥ 5. የእግዚአብሔር ("የያህዌ") መንፈስ (መሳ. 3፡10)፥ 6. መንፈስህ (መዝ. 139፡7)፥ 7. የጌታ እግዚአብሔር መንፈስ (ኢሳ. 61፡1)፥ 8. የአባታችሁ መንፈስ (ማቴ. 10፡20)፥ 9. የሕያው እግዚአብሔር መንፈስ (2ኛ ቆሮ. 3፡3)፥ 10. መንፈሴ (ዘፍጥ. 6፡3)፥ 11. የእርሱ መንፈስ (ሮሜ 8፡11)።

መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚገልጡ ደግሞ አምስት መጠሪያ ስሞች አሉ። እነርሱም፦ 1. የክርስቶስ መንፈስ (ሮሜ 8፡9፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡11)፥ 2. የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ (ፊልጵ. 1፡19)፥ 3. የኢየሱስ መንፈስ (ሐዋ. 16፡7)፥ 4. የልጁ መንፈስ (ገላ. 4፡6)፥ 5. የጌታ መንፈስ (ሐዋ. 5፡9፤ 8፡39) ናቸው። ከነዚህ ጥቅሶች በአንዳንዶቹ ውስጥ የምናገኘው ነገር የሚያመለክተው፥ ከክርስቶስ ስለሆነው መንፈስ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ይሁን ወይ ስለ ራሱ ስለ ክርስቶስ መንፈስ ግልጥ አይደለም። የግሪኩ አባባልም ተመሳሳይ ነው። ምናልባት አብዛኛዎቹ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገሩ ይመስላሉ።

በእነዚህ የመንፈስ ቅዱስ መጠሪያዎች ትርጉም ረገድ አንዳንድ ልዩነቶች ቢኖሩም፥ ሁሉም መንፈስ ቅዱስን እንደ ሦስተኛው የሥላሴ አካልነት፥ ከሌሎቹ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት፥ መለኮትነቱንና ሠራዊነቱን ያረጋግጣሉ።

*ባሕርዩን የሚገልጡ።* የመንፈስ ቅዱስን ባሕርይ ለመግለጥ የሚችሉ ስሞች እጅግ ብዙ ናቸው። ቢያንስ ቢያንስ አሥራ ሰባት ያህሉ መጠሪያዎች መለኮታዊ ባሕርዩን ይገልጣሉ፦

1. የመንፈስ ቅዱስ አንድነት "አንድ መንፈስ" በሚለው ቃል ተገልጧል (ኤፌ. 4፡4)፤ 2. "ሰባቱ መንፈሶች" (በ1980 ዓ.ም. እትም) የሚለው መጠሪያ ፍጹምነትን ያመለክታል (ራእይ 1፡4፤ 3፡1)፤ 3. "መንፈስ ከሚሆን ጌታ" የሚለው መጠሪያ፥ የመንፈስ ቅዱስን ማንነትና ውስጣዊ ባሕርይን ያሳያል (2ኛ ቆሮ. 3፡18)፤ 4. "ዘላለማዊ መንፈስ" የሚለው መጠሪያ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን ዘላለማዊነት ያሳየናል (ዕብ. 9፡14)፤ 5. "የክብር መንፈስ" የሚለው መጠሪያ፥ ክብሩ ልክ እንደ እግዚአብሔር አብና እንደ እግዚአብሔር ወልድ መሆኑን ያመለክታል (1ኛ ጴጥ. 4፡14)፤ 6. "የሕይወት መንፈስ" የሚለው መጠሪያ የመንፈስ ቅዱስን ዘላለማዊ ሕልውና ያሳየናል (ሮሜ 8፡2)። እንዲሁም ሦስት መጠሪያዎች የመንፈስን ቅድስና ያረጋግጣሉ፤ 7. "የቅድስና መንፈስ" (ሮሜ 1፡4) የሚለው መጠሪያ ቅዱስ የሆነውን የክርስቶስ መንፈስ ሊጠቅስ

ይችላል፤ 8. “መንፈስ ቅዱስ” የሚለው መጠሪያ ዋናውና የተለመደው፥ ብዙም ጊዜ የተጠራበት ስሙ ነው (መዝ. 51፡11፤ ማቴ. 1፡20፤ ሉቃስ 11፡13)፤ 9. “ቅዱሱ” (1ኛ ዮሐ. 2፡20)።

ከመንፈስ ቅዱስ መጠሪያዎች አምስቱ፥ እርሱ የጥበብና የመገለጥ መነሻ መሆኑን በመጠኑ ያሳያሉ፦ 10. “የጥበብ መንፈስ” (ዘጸ. 28፡3፤ ኤፌ. 1፡17)፥ 11. “የጥበብና የማስተዋል መንፈስ” (ኢሳ. 11፡2)፥ 12. “የምክርና የኃይል መንፈስ” (ኢሳ. 11፡2)፥ 13. “የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ” (ኢሳ. 11፡2)፥ 14. “የእውነት መንፈስ” (ዮሐ. 14፡17)። መንፈስ ቅዱስ የጸጋ ባሕርይ እንዳለው የሚያመለክቱ ሁለት መጠሪያዎች አሉ፤ 15. “የጸጋ መንፈስ” (ዕብ. 10፡29)፥ 16. “የሞገስና የልመና መንፈስ” (ዘካ. 12፡10)።

*ሥራውን የሚገልጡ።* ባሕርዩን ይገልጣሉ ብለን ከላይ የጠቀስናቸው አብዛኛዎቹ የመንፈስ ቅዱስ መጠሪያዎች ሥራውንም ያመለክታሉ። ከእነርሱም መካከል የክብር መንፈስ (1ኛ ጴጥ. 4፡14) የሚለው መጠሪያ ቅዱሳንን ወደ ክብር የማምጣት ሥራ እንዳለው ያመለክተናል። የሕይወት መንፈስ የሚለው ደግሞ (ሮሜ 8፡2) አዲስ ፍጥረት የማድረግ ሥራውን ያመለክታል። “የቅድስና መንፈስ” (ሮሜ 1፡4)፥ “መንፈስ ቅዱስ” (ማቴ. 1፡20) እና “ቅዱሱ” (1ኛ ዮሐ. 2፡20) የሚሉት መጠሪያዎች ደግሞ የሚቀድሰን (ቀዳሻችን) እርሱ እንደሆነ ያሳየናል። “የጥበብ መንፈስ” (ኤፌ. 1፡17)፥ “የጥበብና የማስተዋል መንፈስ”፥ “የምክርና የኃይል መንፈስ”፥ “የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ” (ኢሳ. 11፡2) የሚሉት ደግሞ ቅዱሳንን በማስተማር በመምራትና በማበርታት የሚሰጠውን ብዙ አገልግሎት ያሳያሉ። “የእውነት መንፈስ” የሚለውም (ዮሐ. 14፡17) ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አሳብ አለው። ጸጋን የሚሰጥና የሚገልጥ መንፈስ መሆኑን የሚያሳዩ መጠሪያዎቹ ደግሞ “የጸጋ መንፈስ” (ዕብ. 10፡29)፥ የሞገስና የልመና መንፈስ (ዘካ. 12፡10) የሚሉት ናቸው።

በተጨማሪ ሥራውን የሚያረጋግጡ ሌሎች ሁለት መጠሪያዎች ለመንፈስ ቅዱስ ተሰጥተውታል፦ 1. የልጅነት መንፈስ (ሮሜ 8፡15) የሚለው መጠሪያው የእግዚአብሔር ልጆች እንሆን ዘንድ ይህን መገለጥ የሰጠን እርሱ መሆኑን ያሳያል። 2. የእምነት መንፈስ (2ኛ ቆሮ. 4፡13) ይህ መጠሪያው ግላዊ ባለመሆኑ መንፈስ ቅዱስን የማያመለክት ይመስላል። እንደሚያመለክት አድርገን ስንቀበለው ግን በውስጣችን እምነትን የመፍጠር ሥራን ያሳያል።

መንፈስ ቅዱስ፥ "መንፈስ" የሚል ቃል የሌለበት ሌላም መጠሪያ አለው። ይህም በግሪኩ 'ጳራቅሊጦስ' ['parakletos'] የሚለው ቃል ሲሆን፥ ታየር [Thayer] እንደተባለው ሰው አባባል ሰፋ አድርገን ያየነው እንደሆነ፥ ትርጉሙ "አጽናኝ፥ ረዳት፥ አጋዥ፥ ደጋፊና ተተኪ የሚሉትን ቃላት በመወከል፥ መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ስፍራ ተተክቶ ከሐዋርያት ጋር እንደሚሆን የሚያሳስብ ነው።" ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን በብዙ ስፍራ ይገኛል (ዮሐ. 14፡16፥ 26፤ 15፡26 ፤ 16፡7)። ክርስቲያኖችን ለመርዳትና ለማገዝ ሁልጊዜ ዝግጁ ሆኖ በተጠንቀቅ የሚገኝ መሆኑን ያሳየናል።

መንፈስ ቅዱስ የተጠራባቸው ስሞች የተለያየ አቅጣጫ ካለው ትርጉም ጋር እጅግ ውብ ስለሆነው አካላዊ ሕልውናውና አስደናቂ ባሕርዩ በግልጥ ይናገራሉ። እነዚህ በተለያየ አመለካከት የተገለጡት እውነቶች፥ ወሰን የሌለው የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውና በኃይልም ሆነ በክብር ከአብና ከወልድ ጋር እኩል መሆኑን ያስረዳሉ።

## 2. ከእግዚአብሔር ጋር ያለው አንድነትና ግንኙነት*

*ከያህዌ ጋር አንድ ስለመሆኑ።* የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት የታየው ከላይ በተመለከትናቸው መጠሪያዎቹ ብቻ ሳይሆን፥ በብሉይ ኪዳን 'ያህዌ' ተብሎ ከተጠራው እግዚአብሔር ጋር አንድ ሆኖ በመገለጡ ጭምር ነው። ሐዋርያት ሥራ 28፡25 እና ኢሳ. 6፡1-13ን በምናወዳድርበት ጊዜ፥ በኢሳይያስ 'ያህዌ' (እግዚአብሔር) እና 'አዶናይ' (ጌታ) ተብሎ የተጠራው በሐዋርያት ሥራ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ ሲጠራ እናየዋለን። ኢሳይያስ 6፡9-10 በሐዋርያት ሥራ 28፡26-27 የተጠቀሰ ሲሆን፥ ይህን ቃል የተናገረው መንፈስ ቅዱስ ነው ይላል። ኢሳይያስ ግን አስቀድሞ ይህን የተናገረው (ያህዌ እና አዶናይ) ነው ብሎታል። እንደዚህ ያለውን ተመሳሳይ ሁኔታ ዕብራውያን 10፡15-17ን ከኤርምያስ 31፡31-34 ጋር በማወዳደር መመልከት ይቻላል። ማለትም በትንቢተ ኤርምያስ ያህዌ የተናገረውን ነገር በዕብራውያን መንፈስ ቅዱስ እንደተናገረው መጠቀሱን እንመለከታለን። ስለዚህ በቅዱሳት መጻሕፍት ለእውነተኛው አምላክ መጠሪያ የሆነውና ያህዌ የሚለው ስም ለመንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶ እናገኛለን።

*ከአምላክ ጋር አንድ ስለመሆኑ።* በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን፥ አምላክ ተለይቶ የሚታወቅባቸው ሌሎች ስያሜዎች፥ መንፈስ ቅዱስም ተጠርቶባቸው እንመለከታለን። በ2ኛ ሳሙኤል 23፡2-3 የእግዚአብሔር ('ያህዌ') መንፈስና የእስራኤል አምላክ አንድ መሆናቸው ተገልጦ

* በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን ተጨማሪ መግለጫ ይመልከቱ።

እንመለከታለን። በብሉይ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ እራሱ እግዚአብሔር ሆኖ መቅረቡ የተለመደ ነገር ነው። የመጀመሪያውን በዘፍጥረት 1፡2 ላይ እናገኛለን። በአዲስ ኪዳንም በተመሳሳይ መንገድ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር መሆኑ የተገለጠባቸው ቦታዎች በርካታ ናቸው። የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆኑት ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ማደሪያ ተብለዋል (1ኛ ቆሮ. 3፡16፤ 6፡19፤ ኤፌ. 2፡22)። መንፈስ ቅዱስን መሳደብ እግዚአብሔርን መሳደብ እንደሆነ ተጽፎ እናገኛለን (ማቴ. 12፡31-32)። በሐዋርያት ሥራ 5፡1-4 በተጻፈው ታሪክ ላይ የሐናንያና የሰጲራ ኃጢአት በእግዚአብሔር አብና በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተሠራ ኃጢአት እንደሆነ እንመለከታለን።

*መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር ያለው ግንኙነት።* መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር በእኩልነት በተደጋጋሚ መጠቀሱ አምላክነቱን ያሳየናል። በማቴዎስ 28፡19 በተሰጠን የጥምቀት መመሪያ (መሠረታዊ ደንብ) ላይ "አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" በእኩል ግንኙነት ተጠቅሰው እንመለከታለን። እንዲያውም "በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም" በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ "ስም" የሚለው ቃል በነጠላ ቁጥር መሆኑ የመለኮት ሙሉ ስም "አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" መሆኑን ያሳያል። ይህ ዓይነቱ ግንኙነት እንደገና በሐዋርያት ቡራኬ ውስጥም ይገኛል (2ኛ ቆሮ. 13፡14)። በእነዚህ ተደጋጋሚ ጥቅሶች ውስጥ የሥላሴ አካላት በእኩልነት ቀርበው እኩል ክብር ሲሰጣቸው ይታያል። ስለዚህ እንደዚህ ዓይነቱ አጠቃቀም እኩልነታቸውን አያመለክትም ብሎ አቋም ለመያዝ መሞከር የሚያስቸግር ነው።

ይህን የመሰለን ግንኙነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዛት ማግኘት ይቻላል። ለምሳሌ፡- ለነቢያት የመገለጥን መልእክት ይሰጥ የነበረ እግዚአብሔር እንደሆነ በዕብራውያን 1፡1 ሲገልጥ፥ በ2ኛ ጴጥሮስ 1፡21 ደግሞ፥ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን እንመለከታለን። በሌላ አነጋገር መንፈስ ቅዱስን አንዳንድ ስፍራ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር፥ በሌሎች ስፍራዎች ከአብና ከወልድ ጋር አገናዝቦ ማቅረብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እጅግ የተለመደ ነው።

## 3. የመንፈስ ቅዱስ ሠራፂነት (መውጣት)

የሠራፂነት መሠረታዊ የእምነት ትምህርት፥ ከአብና ከወልድ ጋር ባለው ግንኙነት መንፈስ ቅዱስ ሕያውና ዘላለማዊ መሆኑን የሚናገር ነው። በሥላሴ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ፥ እንዳለ አንድ ክፍል፥ ይህ የሠራፂነት መሠረታዊ ትምህርት መንፈስ ቅዱስ የሥላሴ ሦስተኛው አካል

ሆኖ ከአብና ከወልድ ጋር በሕልውናና በባሕርይ አንድ፥ በኃይል፥ በዘላለማዊ ሥልጣንና ክብር ደግሞ እኩል መሆኑን ያረጋግጣል። የመሠረተ እምነቱ የተሟላ መግለጫ፥ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ለዘላለም የሠረፀ ወይም የወጣ ነው የሚል ነው።

*የመንፈስ ቅዱስ መሥረፅ እርግጠኛነት።* የሥላሴነቱ መሠረታዊ የእምነት ትምሕርት የተመሠረተው በመጽሐፍ ቅዱስና አጥጋቢ በሆኑ ምክንያታዊ ግንዛቤዎች ላይ ነው። የቀድሞዎቹ የቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫዎች ለተሟላ አቀራረቡ በቂ ትኩረት ሰጥተውት ነበር። ለምሳሌ:- የኒቅያ ጉባኤ የእምነት መግለጫ፥ “ከአብና ከወልድ በሠረፀው፥ ሕይወት ሰጭና ጌታ በሆነው፥ በመንፈስ ቅዱስ እምናለሁ፤ እርሱ ከአብና ከወልድ ጋር ሊመለክና ሊከበር ይገባል” ይላል። የአትናቴዎስ [Athanasius] የእምነት መግለጫ

ደግሞ አጠር ባለ መንገድ፥ “መንፈስ ቅዱስ እንደ አብና እንደ ወልድ ነው፥ እርሱ አልተሠራም፥ አልተፈጠረም ወይም አልተወለደም ነገር ግን የሠረፀ ነው” ይላል። በቅርቡ ደግሞ “ሠላሳ ዘጠኙ የእንግሊዝ አብያተ ክርስቲያናት አንቀጾች” [Thirty Nine Articles of the Church of England] መሠረታዊውን የእምነት ትምህርት* እንዲህ ብለውታል:- “ከአብና ከወልድ የሠረፀው መንፈስ ቅዱስ፥ ከእነርሱ ተመሳሳይ የሆነ ሕልውናና ሞገስ ያለው ከአብና ከወልድ ጋርም ዘላለማዊ አምላክ ነው።”

እነዚህ የእምነት መግለጫዎች፥ የመጽሐፍ ቅዱስን ያህል ስሕተት አልባ ባይሆኑም፥ ክርስቲያኑ ኅብረተሰብ ያለምንም ጥያቄ ተቀብሏቸዋል። መግለጫዎቹ የተጻፉበት መንገድ የተለያየ ቢሆንም፥ መሥረፅ ከመወለድ የተለየና ዘላለማዊ መሆኑን ሁሉም ያረጋግጣሉ።

ይህ መሠረታዊ የእምነት ትምሕርት በሥነ-መለኮት ትምህርት ሊቃውንትና በቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው በቂና ግልጥ የሆነ የቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ስላለው ነው። ይህ የሥላሴነት ባሕርይ ለአእምሮ የሚመችና ለመረዳት የቀለለ ባይሆንም፥ በሥላሴ አካላት ውስጥ ያለውን ግንኙነት ለመገንዘብ የሚረዳ ትርጉም ይሰጣል። ለትምህርቱም እንደ ዮሐንስ 15፡26 እና መዝሙር 104፡30 ያሉት ጥቅሶች ግልጥ የሆኑ መረጃዎች ናቸው። በዮሐንስ 15፡26 ክርስቶስ ሊልክልን ቃል የገባው አጽናኝ “ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ” ተብሏል። “መውጣት (መሥረፅ)” የሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት የመጀመሪያ ቋንቋ፥ ጊዜው ትንቢታዊና ኃላፊ ሳይሆን፥ የአሁን ጊዜ መሆኑ ያለምንም ተቃውሞ ተቀባይነት ስላለው፥ መንፈስ ቅዱስ ከመጀመሪያው

* በቅርብ የተደረጉ ዋና ዋና የእምነት መግለጫዎችን ዝርዝር በመጽሐፉ መጨረሻ ይመልከቱ።

የሥላሴ አካል ጋር ያለውን ግንኙነት ለመገንዘብ የሚረዳ ሆኗል። በመዝሙር 104፡30 የተጻፈው "መንፈስህን ትልካለህ" የሚለው ቃልም ተመሳሳይ መረጃ ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ሠራፂነት እርግጠኛ ስለመሆኑ በተደጋጋሚ "የእግዚአብሔር መንፈስ" እና "የክርስቶስ መንፈስ" ተብሎ ከተጠቀሰው ማረጋገጥ ይቻላል" (1ኛ ቆሮ. 2፡11-12፤ ገላ. 4፡6፤ ሮሜ 8፡9)። ከእነዚህ ሁለት የማረጋገጫ መንገዶች የመንፈስ ቅዱስ ሠራፂነት በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ የእምነት ትምህርት ነው ብሎ ከውሳኔ ላይ መድረስ ይቻላል።

*የመንፈስ ቅዱስ ሠራፂነት ዘላለማዊ ስለመሆኑ።* የመሥረፅን መሠረታዊ ትምህርት ከምናረጋግጥባቸው ነገሮች አንዱ የመንፈስ ቅዱስ ሠራፂነት ዘላለማዊ መሆኑ ነው። ይህን ጉዳይ በሚመለከት የክርስቲያኑ ኅብረተሰብ አስተሳሰብ አንድ ዓይነት አይደለም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥም ይህ ጥያቄ ዋና ዋና የሥነ-መለኮት ትምህርቶች በሚለው ርእስ ጉዳይ ውስጥ ከሌሎች ጉዳዮች ጋር ተነሥቶ ያወዛግብ የነበረ ነው። እስከዛሬም የግሪክ ኦርቶዶክስ [Greek Orthodox] እና የሮም ካቶሊካዊት አብያተ ክርስቲያን [Roman Catholic Church] በዚህ ጉዳይ ስምምነት ላይ ለመድረስ አልቻሉም። የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፥ መንፈስ ቅዱስ የሠረፀው ክርስቶስ ሥጋን በለበሰ ጊዜ ነው በማለት ከክርስቶስ ሥጋ መልበስ ጋር ስታያይዘው፥ የሮም ቤተ ክርስቲያን ግን ሠራፂነቱ ከዘላለም በፊት የሆነ ነገር ነው ብላ ታምናለች። የፕሮቴስታንት [Protestant] አብያተ ክርስቲያናትም ይህን ጉዳይ በሚመለከት ከሮም ቤተ ክርስቲያን አሳብ ጋር ይስማማሉ።

የመንፈስ ቅዱስ ሠራፂነት ዘላለማዊ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ የተደገፈና በእግዚአብሔር ቃል የተረጋገጠ ነው። ከዮሐንስ 15፡26 በእርግጠኝነት የምንረዳው ይህ ግንኙነት ዘላለማዊ መሆኑን ነው። የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ባላት አቋም ላይ ያለው ግልጥ የሆነ ችግር፥ መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ጊዜ በመሥራት ላይ ስለነበር ያኔ መሥረፁ ሐቅነት አለው የሚል መሆኑ ነው (መዝ. 104፡30)። መንፈስ ቅዱስ በፍጥረትም ሆነ ከዚያ በኋላ የነበረ ሥራው ሁሉ ሠራፂነቱን ያረጋግጣል።

የሠራፂነቱ መሠረታዊ ባሕርይ ዘላለማዊነቱን ያሳያል። የመንፈስ ቅዱስ ሠራፂነት ፅንሰ-አሳብ ከመፈጠር፥ በሰው የአስተሳሰብ ክልል ውስጥ ከመሆን፥ በመጀመሪያ ከመኖር (ሕላዌነት) አሳብም ሆነ ከሰው ሰብአዊ ግንኙነት ውጭ የሆነና ለየት ያለ ጭብጥ ነው። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ መሥረፁ (መውጣቱ) ለሕልውናው አስፈላጊ ነበር። ያለ መንፈስ

ቅዱስ እግዚአብሔር ራሱ አሁን ባለው መለኮታዊ ባሕርይ አይገኝም ነበር። የክርስቶስ ሥጋ መልበስ በጸጋ የሚዋሐዱትን የፍቅርንና የጽድቅን ባሕርያት ለመግለጥ የሚያገለግል ቢሆንም፥ የመንፈስ ቅዱስ ሠራፂነት ከክርስቶስ ሥጋ መልበስ ጋር ሊወዳደር አይችልም። የክርስቶስ ሥጋ መልበስ ለመለኮት የማያስፈልግ ነበርና።

*የመሥረፅና የመወለድ ግንኙነት።* የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ሁለተኛውና ሦስተኛው የሥላሴ አካላት ከመጀመሪያው የሥላሴ አካል ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ለመግለጥ የሚጠቀሙበት መንገድ ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ የተወሰደ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ልጁ ሲናገር፥ መወለዱ ለዘላለም እንደሆነ የሚያረጋግጥ ሲሆን (መዝ. 2፡7) ከላይ እንደተመለከትነው ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር ደግሞ መውጣት (መሥረፅ) ይለዋል። ቃላቱ ሊያቀርቡት የሚችሉትን እውነት ለመግለጥ፥ ለመረዳትም በቂ አይደሉም፥ ቢባልም እንኳ የትኛውም የሰው አስተሳሰብ ይህን ልዩነት ሊያሻሽለው አይችልም። ነገር ግን መውለድ የሚለው ቃል በምንም ዓይነት አሁን በምድር ከምናውቀው የመወለድ አስተሳሰብ ነጻና የማይወዳደር መሆኑንና ሠራፂነትም ዘላለማዊ መሆኑን ማስታወስ ይገባል። በተጨማሪ መውለድን ለመሥረፅ ልንጠቀምበት አንችልም፥ ምናልባት ክርስቶስ ከአብ ዘንድ ወጣ ማለት ብንችል እንኳን፥ መንፈስ ቅዱስ ተወለደ ማለት ግን አንችልም።

*የመንፈስ ቅዱስ ሠራፂነት ከአብና ከወልድ ስለመሆኑ።* ስለ መንፈስ ቅዱስ ሠራፂነት ብዙ ጊዜ በታሪክ የሚነሣው አወዛጋቢ ነገር፥ መንፈስ ቅዱስ የሠረፀው ከአብ ብቻ ነው ወይስ ከአብና ከወልድ? የሚለው ጥያቄ ነው። በ325 ከክርስቶስ ልደት በኋላ በኒቅያና፥ በ381 ከክርስቶስ ልደት በኋላ በቁስጥንጥንያ [Constantinople] የተደረጉት የመጀመሪያዎቹ ጉባኤዎች ያወጡአቸው የእምነት መግለጫዎች፥ መንፈስ ቅዱስ የሠረፀው ከወልድም ጭምር መሆኑን ባይገልጡም እንኳ በውስጠ ታዋቂነት የታመነ ነበር። በ589 ከክርስቶስ ልደት በኋላ፥ በቶሌዶ [Toledo] የተካሄደውና የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናትን ብቻ የሚወክለው ጉባኤ ግን፥ ሥርፀት ከወልድም ጭምር [‘ፊሊዮክዌ’/‘filioque’] እንደሆነ የሚናገር ቃል በግልጥ በእምነት መግለጫው ላይ ጨመረ። ይህ ቃል በታከለ ጊዜ ምክር ያልተጠየቀችው የግሪክ ቤተ ክርስቲያን፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ትምህርቱን የማትቀበል መሆኗን ገለጠች። ይህች ቤተ ክርስቲያን ለሥርፀት አሳብ በዋናነት የምንጠቀምበትን የዮሐንስ 15፡26 ቃል ሥርፀት ከአብ ብቻ እንደሆነ ነው የሚናገረው ብላ ተከራከረች። የምዕራብ፥ ወይም የሮም ቤተ ክርስቲያን ግን፥ መንፈስ ቅዱስ የሠረፀው ከአብና ከወልድ መሆኑ ግልጥ ነው በማለት አሳቧን አጸናች። ለዚህም ገላትያ 4፡6 “የልጁ መንፈስ” ሮሜ 8፡9 “የክርስቶስ መንፈስ”

የሚሉ ቃላት በማስረጃነት የሚጠቀሱ ሆኑ። በተጨማሪም መንፈስ ቅዱስ የተላከው በአብና በወልድ ነው በማለት (ዮሐ. 16፡7) በማስረጃነት ቀርቧል። *መሥረፅ* ከአብና ከወልድም ጭምር ነው የሚለው አሳብ የሮምና በተሐድሶ የተገኙት የሌሎች (ፕሮቴስታንት) አብያተ ክርስቲያናት የጸናና ቀጥተኛ አመለካከት ሆኗል።

*የመንፈስ ቅዱስ ሠራፂነት ከሥራዎቹ ጋር ያለው ግንኙነት።* የመሥረፅ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ለሥነ-መለኮት ትምህርት አዋቂዎች ብቻ የሚጠቅም ቴክኒካዊ አባባል ቢመስልም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የሚናገር ዋና አሳብ በውስጡ ይገኛል። ስለ ክርስቶስ ስንመለከት፥ ለዘላለም መወለዱ፥ ጊዜውን ጠብቆ የሰውን ልጅ ለመዋጀት ከሚፈጽመው ሥራ ጋር የተያያዘ ነበር። ክርስቶስ የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም ታዛዥ እንደሆነ፥ መንፈስ ቅዱስም ከአብና ከወልድ በመሥረፅ ለአብና ለወልድ ታዛዥ ሆነ። ክብርን በፈቃደኛነት በመተው ራስን ማስገዛት፥ ሦስቱ የሥላሴ አካላት ለዘላለም የነበራቸውን ክብር ሳይቀንስና የመለኮትነት ባሕርያቸውን ሳያጡ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል (ዮሐ. 14፡16፥ 26፤ 15፡26፤ 16፡7)። የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ስለ አብና ስለ ወልድ የሚደረግ ቢሆንም፥ በራሱ ኃይል ሥራውን ማከናወኑ ዘላለም ላለው መለኮትነትና ክብር ምስክር ይሆነዋል። ስለዚህ፥ መንፈስ ቅዱስ ወደ ዓለም የተላከው በክርስቶስ ቦታ ሆኖ እውነትን ሊገልጥና፥ በተለይ ደግሞ የክርስቶስ ተልእኮ ታውቆ አብና ወልድ እንዲከብሩ ነው (ዮሐ. 16፡13-15)። ክርስቶስ እራሱን ትሑት ባደረገ ጊዜ ክብር እንዳልፈለገ ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስም የራሱን ክብር አይፈልግም።

*የመወለድና የመሥረፅ መሠረታዊ የእምነት ትምሕርት* መግለጫዎችን በወልድና በመንፈስ ቅዱስ *ሥራዎች* ውስጥም ማየት እንችላለን። አብ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን እንደላከ፥ ወልድ መንፈስ ቅዱስን እንጂ አብን ጨርሶ አይልክም። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ሁልጊዜ የራሱ ፈቃድ ለሆነው ለአብና ለወልድ ፈቃድ በመገዛት፥ በምድር ላይ ያለ ሥራውን ከግብ ያደርሳል እንጂ፥ አብንም ሆነ ወልድን አይልክም። የሥርፀት ፅንሰ-አሳብ በቀላሉ የሚገባ ባይሆንም፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መግለጥ በሥላሴ መካከል ያለውን ግንኙነት በሰዎች ቋንቋ የሚያስረዳ ነው።

## 4. የመንፈስ ቅዱስ ባሕርያት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጡት የመንፈስ ቅዱስ ባሕርያት፥ እርሱ ፍጹም አምላክ እንደሆነ በማያሻማ ሁኔታ የሚገልጡ ናቸው። ቢያንስ ሰባት ነገሮችን በመጥቀስ ይህን ለመግለጥ ይቻላል።

1. መንፈስ ቅዱስ የሕይወት ባለቤት እንደሆነ ተገልጧል (ሮሜ 8፡2)። በዚህ ጥቅስ ረገድ የዘላለማዊ ሕይወት አስቀድሞም በእግዚአብሔር ዘንድ ያለ ነበር። አሁን ግን ይህ ሕይወት እግዚአብሔር ፍጥረታቱ በዳግም ልደት መንፈሳዊነት ወይም ዘላለማዊ ሕይወት እንዲኖራቸው ማድረጉን ያሳያል።

2. ከዚህ በፊት እንደተገለጠው የአካላዊ ሕልውና ባሕርያቱ በርካታ ምስክሮች ናቸው፤

3. እግዚአብሔር ብቻ ሊኖረው የሚችለውን በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የመገኘት ባሕርይ መንፈስ ቅዱስም አለው (መዝ. 139፡7)፤

4. መንፈስ ቅዱስ ሁሉን አዋቂ ነው (1ኛ ቆሮ. 2፡10-11)፤

5. መንፈስ ቅዱስ ሁሉን አድራጊ ነው። ይህ በመፍጠር ሥራው ውስጥም ተገልጧል (ዘፍጥ. 1፡2)፤

6. ቅድስና በመንፈስ ቅዱስ ስም ውስጥ መገኘቱ፥ ቅድስና ባሕርይው መሆኑን ያመለክታል (ሉቃስ 11፡13)፤

7. የመንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊነትም በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጧል (ዕብ. 9፡14)። ማንኛውም የባሕርይ መግለጫ ማንኛውንም ነገር ሙሉ ለሙሉ የሚገልጥ አይደለም። ቢሆንም በግልጥ ከቀረቡት ባሕርያቱ የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገባ የታወቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ይቻላል።

## 5. የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች

የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት በሥራዎቹ ውስጥም ይታያል። የዚህ መጽሐፍ አብዛኛው ክፍል በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ የሚያተኩር እንደመሆኑ መጠን፥ እዚህ ነጥብ ላይ መለኮትነቱ እንዴት በሥራው እንደተገለጠ መረዳቱ ብቻ ይበቃል። የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች በሙሉ መለኮትነቱን የሚያመለክቱ ናቸው። የመፍጠር ሥራውን በሥዕላዊ አገላለጥ ለመጥቀስ ይቻላል (ዘፍጥ. 1፡2)። የመፍጠር ሥራ የመለኮት ሥራ መሆኑ ግልጥ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ዳግም የመፍጠር ሥራ ሌላው ሥዕላዊ መግለጫ ነው (ዮሐ. 3፡6)። በመንፈስ ለሞቱ መንፈሳዊ ሕይወትን መስጠት የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። አማኞችን የመቀደስ ሥራውንም መጥቀስ ይቻላል (2ኛ ተሰ. 2፡13)። ያልተቀደሰውን መቀደስ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ምስክርነት እንዳለ የሚቀበሉ ሁሉ በሚሠራቸው ሥራዎች እንደተገለጠው፥ መንፈስ ቅዱስ አምላክ መሆኑን ፈጥነው በቀላሉ ለመረዳት አይቸገሩም። ስለ መንፈስ ቅዱስ መለኮትነት ቻርልስ ሆጅ

በተናገረው ቃል ማጠቃለል ይቻላል፦ "ስለዚህ እርሱ አምልኮ የሚገባው ሆኖ ቀርቧል። በመጽሐፍ ቅዱሳችን የሥላሴን የእምነት ትምሕርት እንደ መሠረታዊ የሃይማኖታችን እውነት ዘወትር እንድናስታውስ ያስገነዝበናል። ይህም በጥምቀት መሠረታዊ መመሪያና በሐዋርያት ቡራኬ ብቻ ሳይሆን፥ ያለማቋረጥ ወደ እርሱ እንድንመለከትና በመንፈሳዊ ጥቅማችን ሁሉ በእርሱ እንድንታመን፥ እንደ መለኮታዊ መምህራችንና ቀዳሻችን እንድናከብረውና እንድንታዘዘውም ነው።"

---

## ከአሳታሚው መግለጫ

ብሉይ ኪዳን የተጻፈው በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲሆን፥ ለእግዚአብሔር መጠሪያ ሦስት ታላላቅ ስሞች መሰጠታቸውን እንግራለን።

በመጽሐፉ ውስጥ እግዚአብሔር በዕብራይስጥ ቋንቋ በተደጋጋሚ 'ኤል' ('El') ወይም 'ኤሎሂም' ('Elohim') በሚል ስም ይጠራል። ኤሎሂም የሚለው ስም የእውነተኛው እግዚአብሔር ወይም የአሕዛብ አማልክት መጠሪያ ሊሆን ይችላል። በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ኤሎሂም የሚለው ስም "God" በሚለው ቃል ይተረጎማል። በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የአሕዛብ አማልክት "አማልክት" በሚል ስያሜ ተጠቅሰው እናገኛለን። እውነተኛው አምላክ ግን "እግዚአብሔር" ወይም "አምላክ" ተብሎ ተጠቅሷል። ይህ ስም ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው በዘፍጥረት 1፡1 ነው። የቃሉ አተረጓጎም አከራካሪ ቢሆንም "ኃያል" መፈራትና መከበር የሚገባው አምላክ የሚለውን አሳብ የሚያጠቃልል ይመስላል። ኤሎሂም የሚለው ቃል ብዛትን የሚያመለክት በመሆኑ የሥላሴን አሳብ ያዘለ ነው። ስለሆነም በዚህ ስም ውስጥ ሦስቱ ሥላሴ ይገኛሉ።

ሁለተኛውና ዋነኛው የእግዚአብሔር ስም በዕብራይስጥ 'ያህዌህ' ('Yahweh') የሚለው ሲሆን፥ ይህ ስም እውነተኛ ለሆነው ጌታ፥ እግዚአብሔር ብቻ የተሰጠ ነው። በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ 'LORD'፥ 'GOD' ወይም 'Jehovah' ተብሎ ተተርጉሟል። በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ "እግዚአብሔር" ተብሎ ይጠራል። "ያህዌህ" የሚለው ስም በተለይ ለእስራኤል ኪዳን የገባውን እና እውነተኛውን የቃል ኪዳን አምላክ የሚያመለክት ነው። ይህ ስም ከፍጥረት ጋር በተያያዘ ሁኔታ በዘፍጥረት 2፡4 ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰ ቢሆንም፥ ትርጉሙ ግን በዘጸአት 3፡13-14 ላይ እግዚአብሔር ራሱ ለሙሴ "ያለና የሚኖር እኔ ነኝ"

በማለት ራሱን የገለጠበት ነው። ይህ ስም እግዚአብሔር ብቸኛና ዘላለማዊ፥ በራሱ ሕልውና ያለው አምላክ ማለት ነው።

የእግዚአብሔርን ልዩ ልዩ ጠባዮች ለማሳየት ከሌሎች ስሞች ጋርም ተቀናጅቶ ይገኛል፤ ይኸውም 'ይርኤ' (ዘፍጥ. 22፡13-14)፥ 'ንሲ' (ዘጸ. 17፡15)፥ "ሰላም" (መሳ. 6፡24)፥ "ጽድቅ" (ኤር. 23፡6)፥ ወዘተ...።

ሦስተኛው በብሉይ ኪዳን በዕብራይስጥ ቋንቋ የምናገኘው የእግዚአብሔር አምላክ ስም 'አዶናይ' ('Adonai') ሲሆን፥ ትርጉሙም "ጌታ" ወይም "አለቃ" ማለት ነው። ይህ ስም በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "Lord" ወይም "Master" ተብሎ ተተርጉሟል። ቃሉ ጌትነትን የሚያሳይ ነው። ብዙ ጊዜ ኤሎሂም ከሚለው ስያሜ ጋር ተቀናጅቶ የሚገኝ ሲሆን (ዘፍጥ. 15፡2)፥ በዚህ አገባቡ የእግዚአብሔርን አለቅነት ወይም ጌትነት አጠንክሮ ያስገነዝባል። እነዚህ የእግዚአብሔር ስሞች በብሉይ ኪዳን ውስጥ በመቀናጀት ተጠቅሰዋል። በቅንጅት ከሚታወቁት ከነዚህ ስሞች ውስጥ "ያህዌህ ኤሎሂም" ወይም "አዶናይ ኤሎሂም" የሚሉት በብዛት ይገኛሉ።

# 3

# መንፈስ ቅዱስ የተገለጠባቸው አምሳያዎች

መንፈስ ቅዱስ የተገለጠባቸው አምሳያዎች በብዙ የሥነ-መለኮት ትምህርት ውስጥ የሚገባቸውን ያህል በቂ ስፍራ የማይሰጣቸው ናቸው። አምሳያዎች በራሳቸው ውሱን ቢሆኑም፥ መሠረታዊ የእምነት ትምህርትን ለማጎልበትና ለመግለጥ መሰጠታቸው ግን ግልጥ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጥ እንደተሰጡ መመሪያዎችና ትእዛዛት፥ የራሳችንን እምነትና የሰዎችን አስተሳሰብ በከፍተኛ ሁኔታ በማከል አምሳያዎችን ለመመልከት መሞከር፥ ተገቢ ባልሆነ መንገድ እንድንጠቀምባቸው የሚያጋልጠን ይሆናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳሉ እንደ ሌሎች ሥዕላዊ መግለጫዎች (ምሳሌዎች፥ ምልክቶች፥ ንጽጽሮችና ነገሮች ወዘተ.) አምሳያዎች እውነትን ለመረዳት የሚረዱን በከፍተኛ ጥንቃቄ ስንጠቀምባቸው ነው። አንዳንዶች ይህን ምክንያት በማድረግ አምሳያዎችን በተወሰነ መንገድ ብቻ ይጠቀሙባቸዋል። ከዚህ አንጻር ስንመለከት፥ ለብዙ ጊዜያት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተገለጡት አምሳያዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው የተጠቀምን ባቸው በጣም የተወሰኑት ብቻ መሆናቸውን እንረዳለን። በዚህ ክፍል በቀረበው የአምሳያዎች ጥናት ግን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቀጥታ ባይገለጡ እንኳን፥ ለግንዛቤ ቀለል ያሉና ምቹ አምሳያዎችም ታክለዋል።

አምሳያዎች መንፈሳዊ እውነትን ለመግለጥ ካላቸው ጥቅም አኳያ በሚገባ አልተገነዘብናቸውም። ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር [Lewis Sperry Chafer] ስለዚህ ጉዳይ ያለን ግንዛቤ መጎልበት እንዳለበት የሚከተለውን ተናግሯል:-

"ማንኛውም ዓይነት የንግግር መግባቢያ የራሱ የሆነና የተረጋገጠ እውነት አለው። ስለዚህ ንግግሩ በቀረበበት ዘይቤ ምክንያት የያዘው እውነት ሊሰጠው ከሚገባው ግምት በታች መሆን የለበትም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ የተለያዩ የአነጋገር ዘይቤዎች ሁሉ በቀጥታ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርጠው አገልግሎት ላይ የዋሉ ስለሆኑ፥ በምንም ዓይነት የሰዎችን አስተሳሰብ የሚወክሉ አይደሉም ብለን የምናስብበት ምክንያት መኖር የለበትም።"

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ በሚያስተምረው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ውስጥ ከተጠቀመባቸው በርከት ያሉ አምሳያዎች ጋር ሲወዳደር፥ ለመንፈስ ቅዱስ የተጠቀመባቸው አምሳያዎች አነስተኞች ናቸው። ቢሆኑም የመንፈስ ቅዱስን መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ትኩረት በመስጠት ለመግለጥ የተሰጡ እነዚህ አምሳያዎች ባይኖሩ ኖሮ፥ ይህን ትምህርት ሙሉ ለሙሉ መረዳት እጅግ አስቸጋሪ በሆን ነበር። ከዚህ በመቀጠል አምሳያዎቹን በዝርዝር እንመለከታለን።

## 1. ኃይልን መልበስ

በሉቃስ 24፡49 ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ "እነሆም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ። እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ" የሚል ትእዛዝ ሰጥቷቸው ነበር። በዚህ ክፍል ክርስቶስ ያመለከተው በጰንጠቆስጤ ዕለት ስለተፈጸመው የመንፈስ ቅዱስ መውረድና የሰዎች በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ልምምድ መሆኑ ግልፕ ነው። በዚህ አገላለጥ የልብስ አምሳያ ሰብአዊ ድካምን የመሸፈን ውጫዊ ባሕርይ የሚያመለክት ሲሆን፥ ተግባሩም ከላይ እንደሚለበስ ልብስ የሚታየው አካል መለኮትን ወክሎ መቅረቡን መጠቆም ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ እውነትን ለመግለጥ የመልበስ አምሳያ በተደጋጋሚ ቀርቧል (2ኛ ቆሮ. 5፡3፤ ኤፌ. 4፡24፤ 6፡11-17፤ ቈላ. 3፡10፥ 12፤ 1ኛ ተሰ. 5፡8፤ ራእይ 19፡8፥ 13-14)። ኤፍ. ኢ. ማርሽ [Marsh] የተባለ የሥነ-መለኮት ሊቅ ይህን አምሳያ ለመግለጥ ባቀረበው ጥልቅ ውይይት ውስጥ እኛ ራሳችን በምንለብሳቸውና (ሮሜ 13፡12፤ ኤፌ. 4፡24፤ 6፡11፥ 14፤ ቈላ. 3፡10፥ 12፤ 1ኛ ተሰ. 5፡8) እግዚአብሔር በሚያለብሰን መንፈሳዊ አልባሳት መካከል ልዩነት እንዳለ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምር አሳይቷል። ኃይልን መልበስ እግዚአብሔር ከሚያለብሰን አልባሳት መካከል አንዱ ነው። ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጋር ተያይዞ እርሱ በውስጣችን ለሚሠራው ሥራ ውጫዊ መረጃ (ማረጋገጫ) በመሆን የተሰጠንን ተልእኮ በብቃት እንድንወጣ የሚያስችለን ይህን ኃይል መልበስ ነው። በሐዋርያት አገልግሎት ውስጥ በሰዎችም ሆነ በሁኔታዎች ላይ የተገለጠው ኃይል ይህ ነበር።

## 2. ርግብ

ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ የተገለጠው የመንፈስ ቅዱስ አምሳያ ርግብ ነበር። በዚያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳያ በክርስቶስ ላይ መውረዱን አራቱም ወንጌላት ገልጠውታል (ማቴ. 3፡16፤ ማር. 1፡10፤

ሉቃስ 3፥22፤ ዮሐ. 1፥32)። ከእነዚህ ክፍሎች በስተቀር ይህን አምሳያ በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ተብራርቶ አናገኝም። በአዲስ ኪዳን የርግብ ስም የተጠቀሰባቸው ሌሎች ሁለት ስፍራዎች አሉ። ክርስቶስ "እንደ ርግብ የዋሆች" (ማቴ. 10፥16) ስለመሆን የተናገረበት ክፍል፥ በቤተ መቅደስ ውስጥ ለመሥዋዕት ይቀርቡ ዘንድ ስለመሸጣቸው (ማቴ. 21፥12፤ ማር. 11፥15፤ ሉቃስ 2፥24፤ ዮሐ. 2፥14፥ 16) የሚናገሩት ክፍሎች ናቸው።

በብሉይ ኪዳን ርግብ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት እንደሆነ ተጠቅሷል። አምሳያነቱም ከመንፈስ ቅዱስም ይልቅ የክርስቶስ ነው። ከጥፋት ውኃ በኋላ በኖኅ የተለቀቀችው ርግብ፥ አንዳንድ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት የሚያሳይ ዓይነተኛ ምሳሌ ተብሎ ይጠቀሳል። ማኪንታሽ [Mackintosh] የተባለ የሥነ-መለኮት ሊቅ ይህች ርግብ "በክርስቶስ ያለውን እረፍትና ድርሻውን የሚያገኝ የታደሰ አእምሮን የምታሳይ ናት" ብሏል። ርግብ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ሆና በግልጥ የቀረበችው በወንጌላት ውስጥ ብቻ ነው።

ርግብ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ሆና ስትቀርብ፥ መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዩ ቢያንስ አራት ነጥቦችን ከተፈጥሮዋ መጥቀስ እንችላለን። እነዚህም፡-

1. ውበት፥ 2. ጨዋነት፥ 3. ሰላም፥ 4. ሰማያዊ ባሕርይና አመጣጥ ናቸው። የርግብን ጠቅላላ ባሕርያት ስንመለከት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ሆና የመቅረቧን ተስማሚነት እንገነዘባለን።

## 3. የመንፈሱ መያዣ

በአዲስ ኪዳን ሦስት ጊዜ የተጠቀሰው 'አራቦን' የሚለው የግሪክ ቃል "መያዣ" የሚል ትርጉም አለው (2ኛ ቆሮ. 1፥22፤ 5፥5፤ ኤፌ. 1፥14)። ይኸውም አንድ ነገር ለማድረግ ቃል መግባት ወይም ቃልን መስጠት ማለት ነው። ታየር የተባለው ጸሐፊ በግሪክ-እንግሊዝኛ መዝገበ-ቃላቱ "ቀብድ" ብሎ ተርጉሞታል። መያዣው መንፈስ ቅዱስ የሚሰጣቸው ስጦታዎች ሳይሆኑ፥ እራሱ መንፈስ ቅዱስ ነው። እርሱ አብ ሊሰጠን ቃል ለገባልን፥ ገና ላልተቀበልናቸው፥ ግን የራሳችን ለሆኑት ወደፊት ደስታችንን ሙሉ ለሚያደርጉልን ስጦታዎች ሁሉ እንደ ቀብድ ነው። ማርሽ ምሳሌ በመጠቀም እንደሚከተለው ገልጦታል። አንድ ሕፃን አባቱ ያወረሰው ንብረት በሙሉ የእርሱ ለመሆኑ ምንም ጥርጣሬ እንደሌለው ሁሉ፥ አሁን ባይጠቀምበትና ባይደሰትበትም እንኳን፥ ሁሉም

ነገር በንብረትነት የእርሱ ለመሆኑ ምንም የሚያጠራጥር አይደለም። እንዲሁም የጌታ ልጆች በመሆናችን እኛም የጌታ የሆነውን እንደ ልጅ የመውረስ መብትና ተስፋ አለን።

መንፈስ ቅዱስ የምን መያዣ ነው ብለን ብንጠይቅ፥ መልሱን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ይሰጠናል። ይኸውም ወደፊት ከእግዚአብሔር የምንቀበለው ማንኛውም በረከት የሚል ነው። ይኸውም በመንፈስ ቅዱስ ሕልውና ተረጋግጦልናል። የእርሱ ሕልውና ዋስትናችን ነው። ርስታችን፥ ደኅንነታችን፥ ክብራችን፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት ክርስቶስን ወደ መምሰል መድረሳችንና ከኃጢአት ክፉ ኃይል ነጻ መሆናችን ሁሉ መንፈስ ቅዱስን በመቀበላችን ተረጋግጧል።

## 4. እሳት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሚገኙ ብዙ ምሳሌዎች፥ እሳትም ለተለያየ ትርጉም ጥቅም ላይ ውሏል። ለምሳሌ ርግብ የክርስቶስም የመንፈስ ቅዱስም ምሳሌ ሆኖ ቀርቧል። ማርሽ የተባለው ጸሐፊ መንፈስ ቅዱስ በእሳት መመሰሉን ከመጥቀስ ሌላ፥ ስድስት ምልክቶችን እንደሚከተለው አቅርቧል:-

1. የእግዚአብሔር ሕልውና ምልክት (ዘጸ. 3፡2)፥ 2. እግዚአብሔር ሰዎች ያቀረቡትን መሥዋዕት የመቀበሉ ምልክት፥ (ዘሌዋ. 9፡24፤ 1ኛ ነገሥት 18፡38፤ 2ኛ ዜና. 7፡1)፥ 3. የእግዚአብሔር ጥበቃ ምልክት (ዘጸ. 13፡21፤ ዘካ. 2፡5)፥ 4. የእግዚአብሔር ቅጣትና ፈተና ምልክት (ሚል. 3፡3፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡7፤ ዕብ. 12፡29፤ ራእይ 1፡14)፥ 5. የእግዚአብሔር ቃል ምልክት (ኤር. 5፡14፤ 20፡9)፥ 6. የእግዚአብሔር ፍርድ ምልክት (ዘሌዋ. 10፡2)።

እሳት አምሳያ ሆኖ የቀረበለት ሰባተኛ ጉዳይ መንፈስ ቅዱስ ነው። በጴንጠቆስጤ እለት መንፈስ ቅዱስ ሥራውን ባከናወነበት ወቅት "እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው። በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው" (ሐዋ. 2፡3)። ወዲያውም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ (ሐዋ. 2፡4)። በዚህ ቦታ እሳት ለምን እንደታያቸውና ትርጉሙ ምን እንደሆነ አልተገለጠም። ከዚህ በፊት የእሳት አምሳያ የተጠቀሱባቸውን ክፍሎች መሠረት በማድረግ፥ ሐዋርያት ከፊታቸው ባለው አገልግሎታቸው እግዚአብሔር አብሯቸው እንደሚኖር፥ እንደሚጠብቃቸው፥ እንደሚያጽናናቸው፥ እንደሚቀድሳቸውና አገልግሎታቸውን እንደሚያጸና ማሳየቱ ነበር ለማለት እንችላለን። በምድረ በዳ አዲስ በተሠራው የመገናኛ ድንኳንም ሆነ፥ ሰሎሞን ባሠራው አዲስ

ቤተ መቅደስ (ዘጸ. 40፥34፤ 1ኛ ነገሥት 8፥10-11) ላይ በማታ እንደ እሳት፥ ቀን ደግሞ በደመና የተገለጠው ዓይነት ሁኔታ በጰንጠቆስጤ ዕለትም መታየቱን እንገነዘባለን። ይህ በፊታቸው ለነበረው አገልግሎትና ምስክርነት እነርሱን ለመለየት የተደረገ ነበር።

በማቴዎስ 3፥11-12 "በእሳት ያጠምቃችኋል" የሚለው ቃል ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚያያዝ አይመስልም። ምክንያቱም ቀጥሎ ያለው ቃል ስለ ክርስቶስ ሁለተኛ መምጣትና "ገለባን በማይጠፋ እሳት ስለማቃጠል ስለሚናገር" (ማቴ. 3፥12) ባለንበት የጸጋ ዘመን የጀመረው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፥ በሺሁ ዓመት መጀመሪያ ከሚኖረው የእሳት ጥምቀት ጋር በተነጻጻሪነት መቅረቡን ከዚህ እንረዳለን።

## 5. ዘይት

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን በእግዚአብሔር ሰዎች ሕይወት ውስጥ ዘይት ትልቅ ስፍራ ነበረው። በማንኛውም ጊዜ ስለ ዘይት ዋነኛ አምሳያነት ስናስብ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ አገልግሎት እንደሚናገር እናያለን። በመገናኛው ድንኳን ውስጥ፥ ቅድስት በተባለው ስፍራ የነበረው መቅረዝ ያለማቋረጥ ብርሃን እንዲሰጥ ያደረገው የወይራ ዘይት፥ የመንፈስ ቅዱስን የመግለጥና የአብርሆት አገልግሎት ያሳያል። ከዘይቱና ከሚሰጠው ብርሃን በስተቀር የክርስቶስን ክብር የሚገልጠው የተለያየ ቅብ የመቅረዝ ማስቀመጫ የኀብስቱ ጠረጴዛ እና ሌሎች እቃዎች ሙሉ በሙሉ ጨለማ በሆነ ስፍራ ነበሩ። ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የመድረሻው መንገድ ገና ቀናና ቀጥተኛ አልነበረም (ዘጸ. 27፥20-21)።

በብሉይ ኪዳን ለመሥዋዕት ይቀርቡ በነበሩ ነገሮች ውስጥ ዘይት ተፈላጊነት ያለው ነገር ነበር። ትልቅ ክፍልም ነበረው። በእህል ቁርባን ውስጥ (ዘሌዋ. 2፥1-16) ዘይቱ ከዱቄት ጋር ከመደባለቁ ሌላ በዱቄቱም ላይ እንዲፈስ ይደረግ ነበር። ሉዊስ ስፔሪ ቼፈር ስለዚህ ጉዳይ ሲጽፍ፦ "ይህ ሁሉ የክርስቶስ ሕይወትና አገልግሎት በልዩ መንገድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ ሲሆን፥ ግንኙነቱ ክርስቶስ በምድር ላይ ሰው ስለሆነ፥ ለተግባሩ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብርታትን እንደሚያገኝ ወይም እንደሚጠነከር የሚያሳይ ነው" ብሏል። ዘይት ለምጻም ከነጻ በኋላ በቤተ መቅደስ በሚፈጸመው ሥርዓት ውስጥም አገልግሎት ላይ ይውል ነበር (ዘሌዋ. 14፥10-29)።

ዘይት ካህናት ለአገልግሎት በሚሾሙበትም ሆነ፥ ለመገናኛው ድንኳን አገልግሎት ለእግዚአብሔር በሚሰጡበት (የምረቃ) ሥነ-ሥርዓት ወቅት ተግባር ላይ ይውል ነበር (ዘጸ. 40፥9-16፤ ዘሌዋ. 8)። ዘይት

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለው ግንኙነት ሊቀ ካህናችን የሆነውን ክርስቶስን ለሚወክለው ለአሮን ብቻ ሳይሆን ለልጆቹም ያገለግል ነበር። ይህ ሁኔታ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በክርስቶስ ብቻ ሳይወሰን ለክርስቲያኖችም እንደሚሆን የሚያሳይ ነው። የመገናኛው ድንኳን፥ መሠዊያውን ጨምሮ በውስጡ ያሉት ነገሮች በሙሉ በዘይት ይቀቡ ነበር። ይህ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ሰውን በመዋጀት ረገድ የሚያከናውናቸውን ሥራዎች ያመለክታል። ዘይት ንጉሥን በማንገሥ ሥርዓት ውስጥ ያገለግል ነበር (1ኛ ሳሙ. 10፡1፥ 16፡13፤ 1ኛ ነገሥት 1፡39፤ መዝ. 23፡5 ወዘተ...)። ይህም በንጉሥነት አገልግሎት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ያለውን ተግባር ይገልጣል።

ዘይት ለምግብነት ማገልገሉ የተለመደ ሲሆን (ራእይ 6፡6) አንዳንዴም ለመድኃኒትነት (ማር. 6፡13፤ ያዕ. 5፡14)፥ አልፎ አልፎም እንደ ገንዘብ ለዕቃዎች ልውውጥ አገልግሏል (1ኛ ነገሥት 5፡11)። በእነዚህ የዘይት አገልግሎቶች ውስጥ የተለየ ትርጉም ለማግኘት አንችልም። በአሥሩ ቆነጃጅት ምሳሌ ውስጥ (ማቴ. 25፡3-8) በባሕላዊ ልማድ ኩራዙ ብርሃን እንዲሰጥ የሚያደርገው ዘይት፥ የመገለጡ መንፈሳዊ ትርጉም፥ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ማመልከት መሆኑ ግልጥ ነው። እንዲሁም በመዝሙር 45፡7 እና በዕብራውያን 1፡9 የተጠቀሰውን "የደስታ ዘይት" እዚህ ላይ ማንሣት ይቻላል።

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ሥዕላዊ በሆነ መንገድ እንደተጠቀሰው፥ ዘይት የሚከተሉትን ተግባሮች የሚያሳይ አሳብ ያዘለ ነው:- የመቀደስ፥ የመግለጥ፥ የአብርሆት፥ የመለየት፥ የመፈወስ እና የመደገፍ። አምሳያዎች ሁልጊዜ ለዋናውና ለእውነተኛው ነገር ጥላ ስለሆኑ እጅግ አጥጋቢ በሆነ መንገድ የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት ይገልጣሉ።

## 6. ማኅተም

በአዲስ ኪዳን ሦስት ጊዜ ያህል መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች የመዋጀት ተግባር ማረጋገጫ ማኅተም ሆኖ ቀርቧል (2ኛ ቆሮ. 1፡22፤ ኤፌ. 1፡13፤ 4፡30)። በእነዚህ ክፍሎች መንፈስ ቅዱስ ማኅተም አድራጊውን ሳይሆን ማኅተሙን ሆኖ መቅረቡ ግልጥ ነው። እግዚአብሔር በአማኙ ውስጥ ማደሩና መኖሩ በአማኝ ውስጥ የመጀመሪያው የመዋጀት ሥራ ሙሉ ለሙሉ ወደ ፍጻሜ ለመምጣቱ ምልክትና ማኅተም ነው። ማኅተም የሚለው ቃል የሚከተሉትን ነገሮች ያመለክታል:-

1. ዋስትናን፥ 2. ደኅንነትን ወይም ጥበቃን፥ 3. ባለቤትነትን፥ 4. ሥልጣንን። ማርሽ በተጨማሪ:- 5. "ማኅተም በሰዎች መካከል

ያለቀለት የንግድ ውልን”፥ 6. የእውቅና ምልክትነትን፥ 7. ምስጢራዊነትን፥ 8. ማስገደድን (ማዘዝን) እንደሚያሳይ አሳብ ካቀረበ በኋላ፥ “ማኅተም በሚያትመው ነገር ላይ ቅርፁን ወይም አሻራውን ይተዋል” ብሏል። እነዚህ ነገሮች በሙሉ በአማኝ ሕይወት ውስጥ ግሩም ፍጻሜ አግኝተዋል። ስለዚህ እግዚአብሔር የመዋጀት ቃል ኪዳኑን እንደሚፈጽም የሚያረጋግጥ መተማመኛና ዋስትና ይሰጣል።

## 7. አገልጋይ

መንፈስ ቅዱስ በሥራው ብዙ ጊዜ የአገልጋይን ስፍራ ይይዛል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያገለግል ዘንድ ወደ ዓለም እንደተላከ ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስም ያገለግላል። ከብሉይ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስን አገልግሎት ለመግለጥ ልንጠቀምበት የምንችለው፥ የአብርሃም አገልጋይ ለይስሐቅ ሚስት እንደፈለገለት የሚናገረውን ታሪክ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን በግልጥ ባያሳይም ተመሳሳይነቱን ለማወዳደር ያገለግላል። የአብርሃም አገልጋይ ለይስሐቅ ሙሽራ ፈልጎ እንዳገኘለት፥ መንፈስ ቅዱስም የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ለሆነው ለክርስቶስ ሙሽራ ይፈልግለታል። ልክ እንደ አብርሃም አገልጋይ ሙሽራዋን በማግኘትና በማዘጋጀት በመጨረሻም ለክርስቶስ በማቅረብ ተልእኮውን በተሳካ ሁኔታ ይወጣል። የአብርሃም አገልጋይ ለይስሐቅ ሚስት ለማግኘት ያለፈበት ዝርዝር ታሪክ ወደ ሩቅ አገር መጓዙ፥ ለሙሽራዋ ስጦታ መስጠቱ፥ ሙሽራዋ ሙሽራውን ለመቀበል ውሳኔ ያደረገችው እራስዋ መሆንዋ፥ በመጨረሻም ሙሽራዋ ሁሉን ነገር ትታ ወደ ሙሽራው መምጣትዋ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ በአሁኑ ጊዜ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ እያመጣ የክርስቶስ ሙሽራ ለማድረግ የሚሠራውን ሥራ አምሳያነት በሚገባ ይገልጣል።

## 8. ውኃ

ውኃ እጅግ በተትረፈረፈ መጠን የመፈጠሩ ሁኔታ ወሰን የማይገኝላቸውን ነገሮች ለመግለጥ ጥሩ ምሳሌ ሆኗል። በዚህ መልኩ ያየነው እንደሆነ፥ በጥፋት ውኃና በቀይ ባሕር የተገለጠውን የእግዚአብሔር ብርቱ ፍርድ ያሳያል። ውኃ በምሳሌነት ያገለገለበት ሁለተኛ አስፈላጊ ነገር፥ በእውነተኛነቱ ተወዳዳሪ የሌለውና መጠነ ሰፊ የሆነ መገለጥ የሚሰጠው የእግዚአብሔር ቃል ነው (ዮሐ. 3፡5፤ ኤፌ. 5፡26)። ውኃ ቅኔያዊ በሆነ የአነጋገር ዘይቤ ታላቅ ሥቃይን፥ ችግርን፥ መከራን፥ ለመግለጥም አገልግሏል (መዝ. 69፡2፥ 14)። በዚህ ስፍራ ልናተኩርበት የተፈለገው ሦስተኛ የውኃ አምሳያ ግን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ሦስተኛ የሥላሴ አካል ሆኖ የቀረበው መንፈስ ቅዱስ ነው።

ከዚህ በታች መንፈስ ቅዱስና አገልግሎቱ በውኃ አምሳያነት የቀረቡባቸውን እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ሁለት ጥቅሶች እንመለከታለን። በዮሐንስ 4፡14 ጌታ ኢየሱስ የሰማርያይቱን ሴት ባነጋገረበት በዚህ ክፍል፡- “እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፤ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ” ብሎ ሲናገር እንመለከተዋለን። ይህን ክፍል ከዮሐንስ 7፡37-39 ጋር በማገናዘብ፥ ጌታ የሚሰጠው ውኃ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን በቀላሉ ለመረዳት እንችላለን። ምክንያቱም በሁለተኛው ክፍል ውኃ የመንፈስ ቅዱስ አምሳያ መሆኑ በግልጥ ቀርቧል፥ “ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፤ በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል፤ ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ። ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና” (ዮሐ. 7፡37-39ን ከሚከተሉት ጥቅሶች ጋር ያወዳድሩ፤ መኃልይ ዘሰሎሞን 4፡12፥ 15፤ ምሳሌ 5፡15-16፤ ኢሳ. 41፡17-18፤ 43፡2፥ 19-20፤ 58፡11፤ ኤር. 31፡12)። በዮሐንስ 4 የታየው የውኃ ጉድጓድ፥ በዮሐንስ 7 የሚፈልቅ ምንጭ ሆኖ እንመለከታለን። ይህ በጰንጠቆስጤ ዕለት የጀመረ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በአሁኑ ዘመንም እንደሚቀጥል የሚያሳይ ነው። ይህ አምሳያ ከመንፈስ ቅዱስ የሚፈልቀው የዘላለም ሕይወት፥ እንዲሁም እጅግ ሰፊ የሆነውን ኃይሉንና የማንጻት አገልግሎቱን ሁሉ ይገልጣል። ስለዚህ ይህ አምሳያ እነዚህን ነገሮች መግለጥ ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ ሆነን መንፈሳዊ በረከት ሁሉ ከውስጣችን እንዲፈልቅ እራሳችንን እንድንሰጥ ሊቀሰቅሰን ይገባል።

## 9. ነፋስ

የነፋስና የመንፈስ ቅዱስ ጠባይ በብዙ ረገድ ተመሳሳይ ስለሆነ፥ ነፋስ አምሳያ ሆኖ በመቅረቡ መንፈስ ቅዱስን በጥሩ ሁኔታ ይገልጠዋል። የነፋስ ኃይል፥ የማይታይ መሆኑ፥ ቁሳዊ ያልሆነ ተፈጥሮውና የተፈጠረበት ታላቅ ዓላማ በመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕልውናና ሥራ ውስጥ ያሉ ታላላቅ ነገሮችን ይገልጣል። ነፋስ በመጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ ከተጠቀሰበት ከዘፍጥረት 8፡1 ጀምሮ በመጨረሻ እስከተጠቀሰበት እስከ ራእይ 7፡1 ድረስ በሁሉም ቦታ የተጠቀሰው በተለመደ መልኩ ሲሆን፥ ሦስት ክፍሎች ብቻ ነፋስን የመንፈስ ቅዱስ አምሳያ አድርገው አቅር በውታል።

በዮሐንስ 3፡8 መንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደትን በሚመለከት ለሚያከናውነው ሥራ በነፋስ ምሳሌነት ተገልጧል። "ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል። ድምጹን ትሰማለህ፤ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም። ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው።" በዚህ ክፍል መንፈስ ቅዱስ ቁሳዊ ተፈጥሮ ስለሌለው ባይታይም መለኮታዊ ተግባሩን በብቃት እንደሚፈጽም የሚያሳይ ገለጣ ቀርቧል።

በሐዋርያት ሥራ 2፡1-2 ነፋስ የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ምልክት ሆኖ እናየዋለን። "በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ። ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው" በዚህ ስፍራ ነፋስ በግልጥ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባይያያዝም፥ ለተፈጸመው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ውጫዊ ምልክት ሆኖ መታየቱ የማያሻማ ነው። ነፋስ "ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ልክ እንደዚሁ ሞላው. . .በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው" (ሐዋ. 2፡4)። ይህ የሚያሳየው የመንፈስ ቅዱስን ብርቱ ኃይል ሲሆን፥ እግዚአብሔር ሥልጣኑን የገለጠው በዚህ መንፈስ መምጣት ነው።

ነፋስ የመንፈስ ቅዱስ አምሳያ ሆኖ የቀረበበት ሦስተኛ ሁኔታ ደግሞ የብሉይ ኪዳን ነቢያት የእግዚአብሔርን ቃል በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው እንደጻፉት በተገለጠበት በ2ኛ ጴጥሮስ 1፡21 ነው። "በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።" በዚህ ክፍል ነፋስ የሚል ቃል ባይገኝም፥ በነፋስ ተገፍቶ የሚንቀሳቀስ የመርከብ ሥዕል በግንዛቤ ውስጥ እንዳለ በቀላሉ ማየት እንችላለን። ከዚህም ነቢያት መልእክታቸውን ይሰጡ ዘንድ አቅጣጫ የሚያሳያቸውና ጉልበትና ብርታትን የሚሰጣቸው የእግዚአብሔር መንፈስ ነበር፤ ከዚህም የተነሣ መልእክታቸው ከእግዚአብሔር እንደነበር ማረጋገጥ እንችላለን።

አምሳያዎችንና ምልክቶችን በሙሉ በአንድነት ያጠቃለልናቸው እንደሆነ፥ አብዛኛው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በግልጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰፍሮ እናገኛለን። በመንፈስ ቅዱስ ተረትቶ እራሱን ያስገዛ አማኝ፥ ከላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነውን ኃይል በመልበስ በመንፈስ ቅዱስ ሕልውና ዋስትና አግኝቶ፥ ተቀድሶና ተቀብቶ ለአገልግሎት ይለያል። የክርስቶስ ኢየሱስን ፍጹምነት መረዳት እንችል ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ቃሉን በሙላት ይገልጥልናል። የተትረፈረፈ ኃይልና ከፍተኛ ዓላማ ያለው መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ይሠራል። እያንዳንዱ አስፈላጊ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አስቀድሞ በተለያዩ አምሳያዎች በመገለጡ፥ ለዚህ ለተከበረና ወሰን ለሌለው አካል ልባችንንና ሕይወታችንን በመስጠት ልናመልከው፥ ልንወደውና፥ ልንታዘዘው ይገባል።